# መ. የተሰየፉለትን ዳር ደንበር ገጸ-በረከት አድርገው እየሰጡና የተሰውላትን አገር እያጠፉ ለማስመለስ የታቀደው አጽም፣

**ከብ/ጄኔራል ኃይሌ መለሰ.**

(ክፍል ሦስት ካለፈው የቀጠለ)

የወያኔዎች የውጭ ተጠሪ የሆኑት ዶ/ር አረጋዊ በረሄ የእኔን ጽሑፍ እያጥላሉ ለመግለጽ ከተጠቀሙበት አንዱ ባድሜንና ለባለውለታቸው የሱዳን መንግሥት አሳልፈው ለመስጠት የከለሉትን 1600 ክ/ሜ በተፈጥሮ ሐብት የደለበ ለም መሬት የሚመለከት ነው። በሁለቱ ግንባሮች የተደቀኑት ፍጥጫወች የየራሳቸው የሆኑ ታሪካዊ ሂደቶች፣ ብሔራዊ ጥቅሞችና የግጭት መነሻ ምክንያቶች ያሏቸው በመሆናቸው በየራሳቸው ባህርያት መገምገም አስፈላጊ ይመስለኛል። በመጀመሪያ የባድሜን ጦርነት እንመልከት።

## መ.1. የባድሜ ጦርነት መነሻ ምክንያቶች፣

ባድሜ በኤርትራና በትግራይ መካከል የምትገኝ አነስተኛ መንደር (አካባቢ) ናት። ለብሔራዊ ጠቀሜታ የሚውል እንዲህ ያለ የተፈጥሮ ሐብት አላት የምትባልም አይደለችም። የታሪክ አሻራዋም ቢሆን ከቋራ፣ መተማና ኦሜድላ ጋራ የሚወዳደር አይደለም። ለእንደዚህ ያለችው አካባቢ ጦርነት መነሻና በመቶ ሽህ ለሚገመቱ ኢትዮጵያዊያን እልቂት ምክንያት የሆነው በሁለቱ የዓላማ አጋሮችና የቃል ኪዳን ጓደኞች (ሻቢያወችና ወያኔወች) መካከል በተፈጠረው መካካድ ነው። በመሠረቱ ባድሜ በሁለቱ መካከል የተደረጉ ብዙ ድብቅ ስምምነቶች ተቆልፈው ከተቀመጡበት ሳጥን አፈትልካ ወጥታ ምልክት የሰጠች በር ከፋች መረጃ ናት ማለት ይቻላል። ወደፊትም በሂደት ጊዜና ታሪክ እየጎለጎለ የሚያወጣቸው ብዙ ሚስጥሮች እንዳሉ የሚያጠያይቅ አይሆንም። ሁለቱ አባትና ልጆች ስለግዛት መካለል ሲወያዩ ወያኔወች ባድሜን ለሻቢያወች ለማስረከብ፣ ለዚያ ማካካሻ የሚሆን ደግሞ ከጎንደር የአስተዳደር ክልል እንዲወስዱ ስምምነት ሳይኖራቸው አልቀረም። ነገር ግን ሁለቱም ባላሰቡት ሁኔታ ላልጠበቁት ስልጣን ከበቁ በኋላ ሁለቱም ያልተጠበቋቸው ብዙ ነገሮችን ያማዘዙ ሁለት ችግሮች ተደቀኑባቸው።

አንደኛው ኢትዮጵያን ለቅርጫ እንደቀረበ በሬ በቁሟ አርደው ሲካፈሉ ከቆዳ ስፋት ጀምሮ በሐብት ክፍፍልም ለሻቢያወች የደረሳቸው በመቁንን ነበር። የወቅቱ ጥድፊያቸው በኤርትራ ነፃ መውጣት እንጅ በግዛት ማስፋፋት ላይ ባለመሆኑ ይህን ያህል ትኩረት አልሰጡትም ነበር። ስሜን ጫፍ አስመራ ሆነው የወያኔዎችን ሰፍቶ የተንጣለለ ግዛት ካዩ በኋላ ግን ሲስሟት ቀርታ ሲነክሷት እንደሚባለው (የማንዴላንና የሙሰቤኔን ጥያቄ አብሮ ያገናዝቧል) ከፍተኛ ጸጸት አሳደረባቸው። የኢትዮጵያን መበለቻ ቻርተር አብረው ላጸደቁት ኦነጎች ተረግጦ መውጣትም ምክንያት ከሆኑት አንዱ ይኸው ነበር። እነሱ ወሎን እናጠቃልላለን ሲሉ ለወለጋ እንኳ ሳይሆኑ ቀሩ ማለት ነው። እነታምራት ላይኔም ድነናል



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የሚሉን የብዙሐኑን እናት አገር አብረን አስተራርደን በደሟ ታጥበናል በማለት ነው። ሻቢያወች ግን ውላቸውን የበለጠ ጠቀሜታ ባለው ድርድር ለማደስ ከበባ ማድረግ ጀመሩ፣ ያም የባድሜ ጦርነት መሆኑ ነው።

ሁለተኛው ችግር ወያኔወች ከጎንደርም አልፈው የወሎንና የአፋርን የአስተዳደር ክልል እንደፈለጉ እያቀኑ ሲሄዱ ባድሜን ከልለው ለመስጠት ግን የእድሜ ገመዳቸውን በጥሶ የሚጥል አደጋ ደቀነባቸው። በዚህም ምክንያት በውላቸው መሠረት ለማስረከብ ፈቃደኛ ቢሆኑም የትግራይን ሕዝብ እስቲ ማን ደፍሮን ባይነት ግትር አቋም አሰልስለው ሽባ ለማድረግ የሚችሉበት ጊዜ እንዲሰጧቸው ሻቢያወችን ተማጸኑ። ሻቢያወች ግን ወያኔወችን አጣብቀው በመያዝ ወደሚፈልጉት ቀለበት እንዲገቡላቸው ስለፈለጉ የጊዜ ስጡን ተማጽኗቸውን ባለመቀበል ጦርነቱን ጀመሩ። ጉድና ጅርባ ከበስተኋላ ነው እንደሚባለው ተራራ ያንቀጠቀጥን ነን እያሉ ሲደነፉ የኖሩትን የወያኔ መሪወች ብርክ ያስያዘ ድልም አስመዝግበው ነበር። እኔ እንደ እነሱ በወገኖቸ እልቂት የምደሰት አረመኔ ባልሆንም በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ለመግለጽ ያህል እነአዲግራትና መቀሌ በሻቢያወች አየር ኃይል ቦምብ ታረሱ። ወያኔወች በመትረጌስ ጥይት እየቆሉ፣ በሳንጃ እየተለተሉና በቦምብ ናዳ እየጨፈለቁ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የዘወትር ግብዣ አድርገው ሲያቀርቡለት የኖሩትን የልጆች መርዶ ሻቢያወች ደግሞ ለትግራይ ወላጆች ልጆችን ማጣት ምን ያህል ከአንጀት እንደሚያንሰፈስፍ የእሱ ልጆች በሌላው ሕዝብ ላይ ሲፈጽሙ የኖሩትን አረመኔያዊ ድርጊት በተመሳሳይ ሁኔታ በራሱ ላይ ፈጽመው አሳዩት። በእርግጥ ሐውዜን ላይ በወገኖቻቸው ሕይወት ድራማ የተጫወቱ አረመኔወች ይኸንም ቢሆን እንደቀጣይ የመደሰቻ ቲያትር አይተውት ሊሆን ይችላል።

እንደሚታወቀው የወያኔወች ተፈጥሮአዊ ባህሪይ ጥቂት ሲያገኙ እንደፊኛ ከመጠን በላይ ተወጥረው መሬት ጠበብችን ብለው መደንከር፣ ትንሽ ሲቀምሱ ደግሞ ሰማይ ተደፋብን ብለው መጯጯህ ጠቃሚ ባህል አድርገው የሚገለገሉበት በመሆኑ አምርረው የጠሉትንና አንዘግዝገው የጣሉትን ኢትዮጵያዊነት መልሰው እንዲያመልኩትና እንዲመኩበት፣ ተራ ጨርቅ ናት ብለው ሲረግጧት የነበረችውን ሰንደቅ ዓላማችንን ደግሞ እንዲማጸኗትና ከፍተኛ ቦታ ላይ ሰቅለው እንዲያውለበልቧት ከመገደዳቸውም በላይ በሕዝብ እንዳይሰማ ከልክለውት የነበረውን ሽለላና ቅርርቶ እንዲሰማ የፈቀዱበት ጊዜ ነበር። በጠላትነት ፈርጀው የዘመቱበትንና ያን ሁሉ ግፍና በደል ሲፈጽሙበት የኖሩትን ሕዝብ ደግሞ የእናት አገርህ ሉአላዊነቷ ስለተደፈረና ዳር ደንበሯ ስለተጠቃ ፈጥነህ ድረስልን ብለው ተማጸኑት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የአንድነት ኃይሎች በቀጣይነት ከሚታዩባቸው ልዩ ልዩ ድክመቶች ዋናው በየወቅቱ አግኝተዋቸው የነበሩትን ድል አስጨባጭ የሆኑ መልካም አጋጣሚወች በአግባቡ ለመጠቀም አለመቻላቸው ነበር። የባድሜ ጦርነት ግን ከማናቸውም በላይ የሆነና እስከመጨረሻው ድረስ ሲያጸጽት የሚኖር እጅግ ከፍተኛ ስህተት የፈጸሙበት ወቅት ነው። በመሠረቱ ያ ጦርነት በአንድ በኩል ወያኔወች ሌሎችን እየቀተሉ ለመኖር በቆለሉት የቃኤል ድንጋይ የእነሱ አናት ተፈጥፍጦ ብትንትናቸው የሚወጣበት፣ በሌላ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በኩል ደግሞ ሊበታትኗት የዘመቱባት እናት አገር ከጥፋት ድና የድል ብሥራቷ ነጋሪት ሊጎሰም የሚችልበት ጦርነት ነበር። እንዲያውም ከጦርነቱ በፊት ከተገኘው ልምድ አኳያ የችግሩን ምንጭ ከስሩ ነቅሎ በማድረቅ የተረጋጋ ሰላም ለመፍጠርና በሁለገብ ማህበራዊ ግንባታ ላይ ብቻ ለመረባረብ የሚያስችል ያልተጠበቁ መልካም አጋጣሚወችን ሁሉ ለአገሪቱና ለሕዝቧ ይዞ የመጣም ነበር። ነገር ግን አገሪቱንም ሆነ ሕዝቧን አጣምረው ለማጥፋትና የራሳቸውን አገርና ዓለም ለመፍጠር አቅደው የተነሱ መሆናቸውን ከጦርነቱ በፊት ባሳለፏቸው ዓመታት በድርጊት ያረጋገጡ  መሆናቸውን ጠንቅቀው እያወቁ እንዲህ ያሉትን ደመኛ ጠላቶች ማህል አስገብቶ ከመደፍጠጥ ይልቅ የበለጠ ተጠናክረው ሲደፈጥጧቸው ለመኖር የሚችሉበትን ኃይልና እድል መስጠት በራስ ጎልውና ላይ ቃላት ሊገልጸው ከሚችለው በላይ የሆነ ወንጀል መፈጸም ነበር፣ የሆነውም ይኸው ነው። በዚያ እጅግ ወሳኝ በሆነ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔዎች ጎን ተሰልፎ ጦርነቱን መደገፍ እንደሌለበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት አርበኞች ኅብረት ግንባር ደጋግሞ ባወጣው መግለጫ አሳስቦ ነበር። ነገር ግን የኅብረት ግንባሩ የሚያካሂደውን አገር አድን የሆነ ሕዝባዊ ዓላማ አሰናክሎ ለማስቀረት በወገን መሰል ጠላቶች ከፍተኛ ዘመቻ የሚካሄድበት ወቅት ስለነበር ጥሪውን የተቀበለው ቀርቶ እህ ብሎ ያዳመጠው እንኳ እንዳላገኘ በገሐድ ሲታይ ውሎ አላደረም። በትምህርት ሰጭነታቸው የምጠቅሳቸው ዋና ዋና ነጥቦች፣

1. ጦርነቱ ከኢትዮጵያ ዳር ደበርና ሉአላዊነት ጋር የሚያገናኝ አንዳችም ነጥብ አልነበረውም፣ የለውምም። ባድሜን ደንበር ማድረግ ግን ወያኔወች በክህደት የቀመሩትን የኤርትራ ቅኝ ግዛትነት ትክክል ናቸው ብሎ መቀበል ነው።

2. ለጦርነቱ መነሻ ምክንያት የሆነው ሁለቱ አባትና ልጆች ወይም ፈጣሪና ተፈጣሪዎች በመካካዳቸው ነው። ስለሆነም በውላቸው ላይ ያልነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህል ገብቶ መተኪያ የሌላቸው ውድ ልጆቹ በፈንጅ እየተቆራረጡ እንዲያልቁ ማድረግ አልነበረበትም። ከዚያ ይልቅ ሻቢያወች በጦርነቱ የበላይነት እንዲያገኙ በሚቻለው ሁሉ መርዳት አስፈላጊ ነበር። ምክንያቱም፣

2.1. የመጀመሪያው ግንባር ቀደም የአገርና የሕዝብ ጠላቶች ወያኔወች እንጅ ሻቢያወች አልነበሩም፣ አይደሉምም። ይህን ስል ሻቢያወች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ያደረሱትን ማናጋትና እልቂት ዘንግቸው አይደለም፣

2.2. ከሻቢያወች ጋር ያለን ቅራኔ ከኤርትራ ጥቅም ጋር ብቻ የተያያዘ ነው። እነሱ ቢያንስ የይገባኛል ጥያቄ የማታነሳ የደካማ ኢትዮጵያን መኖር ይፈልጋሉ። የወያኔወች ስትራተጂያዊ ግብ ግን ኢትዮጵያ የምትባል አገርና ኢትዮጵያዊ የሚባል ሕዝብ በአንድነት እንዳይኖሩ ማድረግ ነው።

2.3 ወያኔዎች በጥርነቱ ግንባራቸው ተፈልጦና ቅስማቸው ተሰብሮ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የልብ ልብ ተሰምቷቸው የአገራችንን ምዕራባዊ የአስተዳደር ክልል ለታሪካዊ ጠላቶቻችን አሳልፈው ለመስጠት አቅደው ባልዘመቱም ነበር።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

2.4. ከትግራይ ሕዝብ ጎን ተሰልፎ ኤርትራውያንን መውጋት ወያኔወችን ሆኖ ኢትዮጵያዊነታቸውን መካድና ሻቢያወች ከመረብ መለስ አሳልፊው ሰጥተውናል እያሉ የሚጠቀሙበትን በክህደት የተቀነባበረ የማስመሰያ ፕሮፓጋንዳ የበለጠ አጉልተው ለመጠቀም የሚችሉበትን እድል ማስፋት ነው።

2.5. የኢትዮጵያ ሕዝብ የባድሜን ጦርነት መደገፍ ማለት የመነጠል አዋጁ ተረቆላትና ቅድመ ሁኔታዎቿ ተመቻችተውላት እውቅና ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ ላለችው ትግራይ አስቀድሞ እውቅና እንደመስጠት የሚቆጠር በመሆኑ ነው። ስለሆነም ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች ተገቢውን ግምት ባለመስጠት ወያኔዎች በጦርነቱ አሸናፊ እንዲሆኑ መርዳት ማለት ጸጸት አርግዞ ሲያምጡ መኖር ብቻም ሳይሆን አገር አጥፊና ሕይወት ቀሳፊ የሆኑ በሽታዎችን በእናት ላይ እንደመርግ ተሸክሞ ሲደፈጡጡ መኖርም ነበር፣ የሆነውም ይኸው ነው። ይህን ስል ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ እድል በዚህ ብቻ ተወስኖ ይቀራል ማለት አይደለም። አሁንም ቢሆን ምን ያህል እንጠቀምባቸዋለን የሚለው ካላጠያየቀን በስተቀር ሌሎችም አዳዲስ መልካም አጋጣሚዎች ዙራቸውን ጠብቀው እንደሚመጡ እርግጠኛ ነኝ። እየመጡም ነው። ከመሠረታዊ ችግሮቻችን ግቃለያ እርምጃዎች አንዱም ከኤርትራውያን ወገኖቻችን ጋር ወደፊት ሊኖረን ከሚገባው ግንኙነት ጋር የተያያዘ ነው። አዎ! በእርግጥ ይኼ ሀሳብ እንደ ፖለቲከኞች አርቆ በማየት በውል ካለተገነዘብነው ብዙ ኢትዮጵያውያንን ሊከፋፍል እንደሚችል በደንብ ይገበኛል። አንድ ሀገርና የአንድ ሀገር ሕዝብ አጥብቆ ማሰብ ያለበት ስለሀገሩ ቋሚ ጥቅም እንጅ ቋሚ ጠላት አለኝ ብሎ መደምደም የለበትም። ትናንት በጠላትነት ተፈርጆ የነበረ ሀገር በጊዜ ሂደት ስትራቴጂካዊ ወዳጅ የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም። ከዚህ ስትራቴጂካዊ ግንዛቤ በመነሳትና ከግል ማኅበራዊ ግንኙነት ጀምሮ የሁለቱን የአንዲት እናት አገር ልጆች የወደፊት ዕድል የሚወስኑ ጉዳዮች ሁሉ መታየት ያለባቸው ከስሜታዊ አመላካከት በራቀ ሰፊ አድማስ ላይ ሆኖ መሆን አለበት። ሌላው ቢቀር ማባባድ፣ ማዳማትና ጠላትነትን መትከል ተልኳቸው የሆኑት ወያኔዎች ያጠሩብንን መሰናክል እንደ ጀርመን ግንብ አፈራርሰን እኛው እራሳችን በቀጥታ መገናኘት የምንችልበትን አመች ሁኔታ መፍጠርና ማጠናከር የግድ ነው። ይህ ደግሞ ለወያኔዎች መቅሰፍት የሆነ እርምጃ መሆኑ ሊያጠራጥረን አይገባም።

በውል መረዳት ያለብን የኤርትራ ሕዝብ ከ60 ዓመታት በኋላ ወደኢትዮጵያዊነቱ ተመልሶ የነበረው ኢትዮጵያ ስለነበረች ነው። ወደፊትም ቢሆን ኢትዮጵያ እስከአለች ድረስ ኤርትራም ትኖራለች። በእርግጥ ኢትዮጵያ እንዳትኖር ለማድረግ አቅደው የዘመቱ ደመኛ ጠላቶች ተሸክሞ እየጎበጡና እየደቀቁ ስለኤርትራ መናገር ግራ መጋባት እንጅ የሚነጋገሩበትን ቁም ነገር ለይቶ ማወቅ መስሎ የማይታያቸው ወገኖች ሊኖሩ ይችላሉ። እኔ ግን የችግሩ ምንጭና የመፍትሄው ግኝት አንድ ስለሆነ ሁለቱን በተመሳሳይ ችግር የሚታመሱ የአንዲት እናት አገር ሕዝቦች ለያይቶ ማየት የለብንም የሚል አቋም ነው ያለኝ። ፕ/ር ሹመት ሲሻኝ በሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች መካከል ያለውን ባለብዙ መልክ ትስስር ሲገልጹ "ተጣብቀው በተወለዱ ህጻናት የሚመሰሉና ይኸኛው ተቆርጦ ይጣል ብሎ ለመወሰን በእጅጉ የሚያስጨንቅ መሆኑን" አስምረው ገልጸውታል። በዚህ ችግር ምክንያት



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የጎረፈው ደም፣ የረገፈው አጽምና ያለፈው ሕይወት አስገኝቷል ከሚባለው ነፃነት አኳያ ሲገናዘብ የሰጠው ትምህርትና ልምድም ቀላል አይደለም። ስለዚህ ይህን ሁሉ የማይረሳው አምላክ ከሚሰጠው ፍርድ በተጨማሪ ሁለቱም ወንድማማች ሕዝቦች ችግሩ ባስተማራቸው ልምድ ታግዘው የሚሰጡትን የጋራ ውሳኔ የሚጠብቅ ገና ያልተዘጋ ፋይል ነው ብየ አምናለሁ።

በመሠረቱ ስለኤርትራ ያለፈ ችግር መደረት ለብሔራዊ ችግራችን መፍትሄ አይሆንም። ከዚህ ይልቅ መቀራረቡ ምን ጠቀሜታ እንዳለው በሰፊ አድማስ ማሰስ በእጅጉ አሰፈላጊ ይመስለኛል። ከዚህ አንጻር ከኤርትራውያን ጋር መቀራረብ ሊያስገኝ የሚችለው ጠቀሜታ፣

1. የመለስ ዜናዊ ራዕይ ጨልሞና ስትራተጂያው ግቡም መክኖ እንዲቀር የሚያደርግ ነው፣

2. ወያኔዎች በኢትዮጵያና በኤርትራ ሕዝብ መካከል የተከሉትን በክህደት ማገር የተጠላለፈ የጠላትነት አጥር ከስሩ ነቅሎ በመጣል ሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች በቀጥታ እንዲገናኙ ማድረግ የሚያስችል ነው፣

3. ተቀራርቦ መወያየት የችግሮች ሁሉ መፍቻ ዋነኛ ቁልፍ በመሆኑ የአጭር ጊዜ ቅርርቡ ወደ ዘለቄታዊ መፍትሄ የሚያመሩ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻች የሚያስችል ተስፋ በውስጡ ያለበትም ነው፣

4. ለወቅታዊ ችግራችን መቀረፍ በመጠኑም ቢሆን አስተዋጽዖ ሊኖረው ይችላል የሚል ግምትም አለኝ። እንዚህን የመሰሉ መልካም አጋጣሚዎች በስፋት አገናዝቦ በአግባቡ አለመጠቀም ግን በባድሜ ጦርነት የፈጸሙትን ስህተት እንደገና መድገም ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ካለፈው ድክመታቸው በመማር በምንም ምክንያት ይሁን መቸና የት፣ ለወያኔወች መሳሪያ ሆነው በኢርትራዊያን ላይ እንደበታቸውን መጠቀምና እጃቸውን ማንሳት እንደሌለባቸው በዚህ አጋጣሚ አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ። የኢትዮጵያውያን የዘወትር ጥረት ማትኮር ያለበት ወያኔዎችን የራሳቸው ሴራ ስራይ ሆኖ ጤና እንዲነሳቸው፣ በየቦታው የከሰከሱት መርዘኛ እሾህ እንሱን ብቻ እየለየ እንዲወጋቸው፣ አጥብበው የአጠሩት አጥር እነሱን ብቻ አጥሮ መፈናፈኛ እንዲያሳጣቸው ወዘተ ማድረግ ነው። ሥራ በሠሪው እሾህ በአጣሪው ላይ ተመልሶ መዋሉ አይቀርም የሚባለውም በዚህ መልኩ ሲገለጽ ነው። ወያኔዎች የዓይናችሁ ቀለም አላማረንም እያሉ በሰዎች ማህበራዊ ደህንነት ላይ በዘመቱ ቁጥር መሳሪያ ሆኖ አብሮ መዝመቱም ማክተም አለበት። በአጠቃላይ ግን ለእኔ ከወያኔወች ወዳጅነት ይልቅ የሻቢያወችን ጠላትነት እመርጣለሁ። ይህን የምለው በአጉል ጥላቻ ተገፋፍቸ ሳይሆን በብዙ ታሪካዊ መረጃዎች ተደግፌና በብዙ መሠረታዊ ምክንያቶች አረጋግጬ ነው።

1. በምዕራባውያን ቅኝ ገዥወች ስር ወድቀው ለ60 ዓመታት ያህል በሚሰቃዩበት ዘመን ኢትዮጵያዊነታቸውን ያልካዱት ኤርትራዊ ኢትዮጵያዊያን፣ **“እኛ እኮ የምንታገለው ቅኝ ገዥወች የወሰዱብንን ኢትዮጵያዊነት ለማስመለስ ነው”፤ “ጥጃዋን ከታሰረችበት ፈትታችሁ ልቀቋት፣ እናቷን ፈልጋ መገናኘቱን እሷ ታውቅበታለች”** እያሉ ተናንቀው



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ለኢትዮጵያዊነታቸው በቅተው የነበሩትን ወገኖቻችን መቸም ይሁን ምን የሚረሳ ህሊና የለኝም። በወያኔወች ሠፈር ግን የእነዚያን ታሪክ ሠርተው ያለፉ ታላቅ ሰወችን ተጋድሎ አምኖ የተቀበለ ቀርቶ በወሬ ደረጃ እንኳ ሰምቻለሁ ብሎ የተናገረ አላየሁም፣ አልሰማሁምም። እንዲያውም የራሳቸውን አባቶች የተጋድሎ ታሪክ በቅኝ ገዥ ወራሪነት ከመፈረጅ ጀምሮ ኤርትራዊያን ቀርቶ እኛ እንኳ አብረናችሁ አልኖርንም እስከማለት የደረሱ፣ ኤርትራዊያን ያልካዱትን ኢትዮጵያዊነት ክደው ያስካዱና ሻቢያዎች ተደራድረው ለመግባት የነበራቸውን እቅድና ፍላጎት ሁሉ አስለውጠው ኤርትራን እስከማስገንጠል ያደረሱ መሆናቸን በራሳቸው ምስክርነት ያረጋገጡ በመሆናቸው ነው። በዚህ መቸውንም ቢሆን በማይረሳ ክህደታቸውና የለየለት ጠላትነታቸው በታሪክም ሆነ በትውልድ ስንፋረዳቸው እንኖራለን።

2. ለወቅቱ ችግር መፈጠርም ሆነ እየተወሳሰበ መጥቶ ከዚህ ደረጃ ላይ መድረስ መሠረታዊ ምክንያት ምንና እነማን እንደሆኑ በመጠኑም ቢሆን ስለማውቅ ነው። ሌላው ቢቀር ከመጡ በኋል "**ኢትዮጵያ አንችን ብየ መጣሁ አንችን አጣሁ**" የሚያሰኝ ችግር ስለአጋጠማቸው እነሱ በህሊናቸው ሸፍተው ልጆቻቸውን በአካል እንዲሸፍቱ እስከማድረግ የደረሱበት ችግር እንደነበረባቸውም ታሪክ መዝግቦት አልፏል። በእርግጥ በዚህ ችግር ላይ የሚያጠያይቅ ነጥብ ቢኖር ለዘመናት ሲታገሉለት የኖሩለትን ኢትዮጵያዊነት እስከ መካድ የሚያደርስ መሆን ነበረበት ወይ? የሚለው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የኢትይጵያ ችግር ብዙ ውስብስብ ባህሪይ ስለአለው ወቅቱ ከፈጠራቸው ገጠመኞች ጋር ተጋግዘው መሆን የማይገባውን እንዲሆን አድርገውታል። አባባሌን በተቃውሞ መልክ የሚያዩት ቢኖሩ ግን በእጅጉ የማከብራቸውና የማደንቃቸው አቶ ዘውዴ እረታ <u>**የኤርትራ ጉዳይ**</u> በሚል ርእስ ስለኤርትራ የጻፉትንና ለህያው ታሪክ ምስክርነት የበቃውን መጽሐፍ አንብበው መረዳት ይችላሉ። ከዚህ ችግር ጋር አዛምጀ ልገልጽው የምፈልገው አሳዛኝ ድርጊት ቢኖር አቶ አክሊሉ ሐብተ ወልድን የመሰሉ ታላቅ የዲፕሎማሲ ሰው መተካት ቀርቶ መከትል እንኳ በማይችሉ ግርግር ፈጣሪዎች መገደላቸው ነው።

3. የሻቢያወች ጠላትነት በብዙ መልኩ ሊያስተናግዱት የሚቻልና ብዙ አማራጭ መፍትሄወችም ያሉት ነው። የወያኔወች ጠላትነት ግን ብዙ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ከብዙ ዓይነት የመበከያ መርዞቻቸው ቀምመው ያዘጋጁቸው የሁለመናችን መበከያ መርዞች ናቸው። ስለዚህ እንደተቀመሙበት የመርዝ ዓይነት መድሐኒቱን ለማግኘት ያኑ ያህል ከባድና ውስብስብ ይሆናል፣ ሆኖዋልም። እነሱም በእቅዳቸው መሠረት ጨርሰው ለማጥፋት፣ እኛም በግፍ ላለመጥፋት የምናደርገው ጥረት በአንዳችን አሸናፊነት አልደመደም ያለውም በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ።

4. ፍቅርን ለመገንባትም ሆነ ጥላቻን ፈጥሮ ለማስፋፋት ይነስም ይብዛ መነሻ ምክንያቶች ያስፈልጋሉ። ከዚህ አንጻር በኤርትራ ውስጥ ለተፈጥረው ችግር መሠረታዊ ምክንያቱ ምንና እነማን እንደሆኑ ከታሪክ ማህደር ያገኘሁትን መረጃ ዋቢ በማድረግ ጠቅሻለሁ። በትግራይ ውስጥ ለተፈጠረው ችግር ግን በዚህ ምክንያት ነው ሊባል የሚችል መሠረታዊ ችግር እስከ አሁን አላገኘሁም። በተለይም በአገሪቱና በሕዝቧ ላይ ይህን ያህል ማናጋትና



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

እልቂት እንዲፈጽሙ የተገፋፉበት ምን ውሎ ያደረ ቂምና በቀል ቢኖራቸው ነው? ብየ እራሴን በጠየቅሁ ቁጥር ያገኘሁት መልስ ከሌሎቹ የምንበልጥ ወርቅ ሕዝብ ስለሆን የማንቀላቀላቸውን አፈሮች እየበተን አጥፍተን እኛ ብቻ መኖር አለብን ብለው በአገሪቱና በሕዝቧ ላይ በእብሪት ጥፋትን ያወጁ የጥፋት መልዕክተኞች ቢሆኑ ነው የሚል ግምት ከማሳደር ባለፈ በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል ብየ ልቀበለው የምችል አንድም ምክንያት አላገኘሁም። እንዲያውም፣

4.1 ከሌሎቹ ክ/ሀገሮች በተለይ የልዑል ራስነት ማዕረግ በተሰጣቸው የራሳቸው ሰዎች ሲገዙም ይባል ሲተዳደሩ የኖሩት እነሱ ብቻ ናቸው። ቅሬታ ኖሮኝ ያን ለመግለጽ ሳይሆን ለማነጻጸር ያህል ለግማሽ ምዕት ዓመት ያህል በኖረው የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ መንግሥት ጎንደሬ የሆነ ጎንደርን ያስተዳደረበት ወቅት አልነበረም። የሌሎቹም ቢሆን ከዚህ የተለየ አይደለም።

4.2 በደርግ መንግሥትም ከሌሎቹ ክ/ሀገሮች በተለየ የራስ ገዝነት ሥልጣን ከተሰጣቸው አንዱም ለእነሱ ነበር። እንሱ ግን የአገሪቱን አካል የሚቆራርጥና ሕዝቧን የሚያቆራርጥ እንጅ እራሳችንን መግዛት የሚችል እራስ ስለሌለን አንፈልገውም ብለው የጣሉት እነሱ ናቸው።

4.3. የትግራይን ክ/ሀገር በግል ከመያዛቸው በተጨማሪ ወደ ሌሎቹ ክ/ሀገሮች ተሠማርተው የፈለጉትን የሥራ ዓይነት እየሠሩ ለመኖር ምንም ዓይነት አድልወም ሆነ ገደብ ሳይኖርባቸው ተስፋፍተው የኖሩና ተደላድለው የተጠቀሙም እነሱ ናቸው። እንዲያውም በአንዳንድ ከተሞችማ ቁልፍ የሥራ ቦታዎችንና የንግድ መናኸሪያዎችን በሞኖፖል ይዘዋቸዋል ከመባል የደረሱበት ወቅትም ነበር። እንዳሁኑ አጠቃለው ከመያዛቸው በፊት ማለት ነው።

4.4 በመሠረተ ልማትም ቢሆን የአካባቢው ተፈጥሮአዊ ሁኔታ በፈቀደው መጠን የተነፈጉት አልነበረም። እንዲያውም ክ/ሀገሩ ከሌሎቹ በተሻለ ደረጃ ላይ ይገኝ እንደነበር የእውነት ዋቢ ሆኑት አቶ ገብረ መድህን አርዓያ ያረጋገጡት ሐቅ ነው።

5. የአንድ አገር መንግሥት ሊኖረው ከሚገባው ሥነ-ባህሪይና የሞራል ብቃት መስፈርቶች አኳያ ሁለቱም ሲገመገሙ ሻቢያወች ለቆሙላት ኤርትራ ብሔራዊ ጥቅም መጠበቅና ዳር ደንበሯ መከበር ከየመን፣ ከሱዳን ከወያኔወችና ከጅቡቲ ጋር ተፋልመዋል። የኤርትራም ሕዝብ ለእኛና ለአገራችን የቆመ መንግሥት አለን ለማለት የሚያስችለው የሥነ-ልቦና ጉልበት አለው። የኤርትራን የአስተዳደር ክልልም ሆነ ጥቅም ለጠላቶቻችን አሳልፎ ሊሰጥና ሊሸጥ ይችል ይሆን የሚል ጥርጣሬም ሆነ ስጋት ፈጽሞ የለበትም። በሁለቱ መካከል ያለው ግጭት (ቅራኔ) የመንግሥት ባህርያት ከሆኑት በአንዱ ማለትም ከአምባ-ገነንነት በሚመጣ ችግር ብቻ ነው። ወያኔወች ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ባይሆኑም እንደ መንግሥት ነን ባይነታቸው የሚገዟትን አገር የባህር በር የዘጉ፣ ፀንቶ የኖረውን የብሔራዊ አንድነት መሠረት ያናጉ፣ ለምና ሰትራቴጂካዊ መሬቶቿን ዘላለማቸውን ሊያጠፉን ለሚጥሩ ታሪካዊ ጠላቶቻችን (ግብጽ እና መሰል ሀገሮች) እየሸነሸኑ የሸጡና አሳልፈው



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የሰጡ ታሪክና ትውልድ የማይረሳቸው ጠላቶች በመሆናቸው ነው። ስለዚህ ያለምንም ምክንያት የአገሪቱና የሕዝቧ አጥፊ ጠላት መሆን አለብን ብለው ጠላትነትን ብቻ ያለአማራጭ ያቀረቡልን በመሆናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት እንዲህ ያሉትን አቻ የለሽ ደመኛ ጠላቶች ከኢትዮጵያ ምድር ጨርሶ ለማስወገድ ከማናቸውም በላይና በፊት ቅድሚያና ትኩረት ሊሰጡት ይገባል።

## መ.2. ለድርቡሾች ገጸ-በረከት ሆኖ ስለተሰጠው የአገሪቱ ምዕራባዊ የአስተዳደር ክልል፣

በዚህ ጽሐፍ መግቢያ እንደገለጽኩት የወያኔዎች አምባሳደር የሆኑት ዶ/ር አረጋዊ በረሄ ከባድሜ ጋር አመሳስለው ያቀረቡት ሌላው ነጥብ ለታሪካዊ ጠላቶቻችን ገጸ-በረከት አድርገው ለመስጠት የከለሉትን የአገሪቱን ምዕራባዊ የአስተዳደር ክልል ነው። ይህ አካባቢ በመልካ ምድራዊ አቀማመጡ ከጎንደር እስከ ጋምቤላ 1600 ኪ/ሜ እርዝመትና እስከ 60 ኪ/ሜ ጥልቀት ያለው ሰፊ መሬት ነው። ይህም ማለት በአገሪቱ ማህል ለማህል አቋርጦ ቢያልፍ ከጎንደር ሐረርጌ ወይም ሞያሌ፣ ጥልቀቱ ደግሞ ከአዲስ አበባ ሞጆ አካባቢ ማለት ነው። ይህ አካባቢ በስፋትና ጥልቀቱ ብቻም ሳይሆን በተፈጥሮ ሐብትም የበለጸገና ለአገሪቱ ብሔራዊ የኢኮኖሚ ግንባታ በከፍተኛ ተስፋ የሚታይ አካባቢ ነው። በታሪካዊነቱ ሲታይ ደግሞ እስከ አሁን ትውልድ ያልተካቸው ታላቁ ንጉሥ አጼ ቴዮድሮስ የተወለዱበትና አጼ ዮሐንስ ከሠራዊታቸው ጋር ዘምተው አንገታቸውን የተሰየፉበትና ቀይ ደማቸውን አፍስሰው ያራሱት አካባቢ ነው። በስትራተጂያዊ ግንዛቤው ደግሞ የጣና ሐይቅና የአባይ ወንዝ መቃረቢያ ከመሆኑ በተጨማሪ ይህን የሚያውቁ ታሪካዊ ጠላቶቻችን የስትራተጂያዊ ግባቸው ማዕቀፍ አድርገው ሲድሁበት እንደኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ጠንቅቀው የሚያውቁት ይመስለኛል። ለዚህም ነው የግብጽ ኤምባሲ አዲስ አበባ ተቀምጦ የሁለቱን መጋቢ ወንዞች ፍሰት ሲያጠና ከኖረ በኋላ ጥናታዊ እቅዱን ለማሟላት ባህር ዳር ከተማ የመቆጣጠሪያ ጣቢያ አቋቁሞ ምንጩን እንዲቆጣጥር፣ የሱዳን መንግሥት ደግሞ ከዳር ወደማህል እየገፋ እንዲሄድ በሦስቱም የተማከለ ግብ አጋሮች እቅዱ ተቀነባብሮ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን በገሐድ እያየን ነው። ስለሆነም ወያኔወች እነዚህን ሁሉ እያወቁ አፄ ዮሐንስ አንገታቸውን በድረቡሾች ያጡበትን ቦታ የጠላትነት ሸንኮፋቸውን ምንጊዜም ከኢትዮጵያ ላይ ለማይነቅሉት ድርቡሾች ለማስረክብ ቁርጠኛ ሆነው የዘመቱበት መሠረታዊ ምክንያት ምንድነው የሚለው ጥያቄ በጥልቀት መመርመር ያለበት ይመስለኛል።

ተደጋግሞ ሲነገር እንደሰማሁት ወያኔወች ያን አካባቢ አሳልፈው ለመስጠት የፈለጉት ተቃዋሚ ኃይሎች በዚያ አካባቢ እንዳይንቀሳቀሱ በሩን ለመዝጋት ብለው ነው ይባላል። እርግጥ ከምክንያቶቹ አንዱ መስሎ ሊታይ ይችል ይሆናል። እኔ ግን በችግሩ ከተፈተነ ልምዴ በተጨማሪ በሽህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እየተገደሉ አሸዋ ውስጥ ተቀብረው ከቀሩበትና ለአረመኔ ጠላቶቻቸው ተላልፈው እየተሰጡ ከታረዱበት መሠርታዊ ችግር ጋር ሳገናዝበው መሆን ቀርቶ መሰልነቱ እንኳ የማይመስል ነው። ምክንያቱም ለረጅም ዘመናት



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ሲካሄድ የኖረውን መበቃቀል ወደጎን አቆይተን የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ በየአንጻሩ ብንገመግም እንኳ ሱዳኖች ከዚህ ወቅት የበለጠ መልካም አጋጣሚና ከአማቻቸው መለስ የቀረበ ታማኝ የቅርብ ቤተሰብ ኖሮ የአንድነት ኃይሎችን ብናቅፍ የበለጠ እንጠቀማለን ብለው ያደርጉታል የሚል እምነት ቀርቶ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት እንኳ ስለሌለኝ ነው። ሌላው ቢቀር ዘርተው ያበቀሏቸው፣ ኮትኩተው ያሳደጓቸውና አስታጥቀው አዝምተው ከዚህ ደረጃ ላይ ያደረሷቸው እነሱ መሆናቸው እየታወቀ ያን ሁሉ የረጅም ጊዜ ጥረት ውጤት ዋጋ አሳጥተው ለብሔራዊ አንድነታቸውና ዳር ደንበራቸው መከበር ለሚታገሉ ኃይሎች ይሰጣሉ ብሎ ማመን ፈጽሞ ስለማይቻል ነው። ይልቅየ እንዲህ ያለው አቀራረብ በድብቅ ለሚያካሂዱት መሠረታዊ ችግር ግርዶሽ ሆኖ የመፍትሂውን ውል እያወሳሰበ በቀላሉ እንዳይፈታ ስለሚያደርግ በብርቱ ሊታሰብበት ይገባል እላለሁ። እኔ ግን ከዚህም የሰፋና የጠለቀ ሚስጥር አለበት የሚል ከፍተኛ ጥርጣሬ አለኝ። ጥርጣሬየም ጥላቻ ፈጠር ግምት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃዎች የተደገፈ ነው። ከመረጃወቹም ዋና ዋናወቹ፣

1. ሁለቱንም ግንባር ፈጥረው እንዲዘምቱ ያደረገ አንድ መሠረታዊ ስትራተጂያዊ ግብ ስለአላቸው ነው። እሱም ኢትዮጵያ የምትባል አገርና ኢትዮጵያዊ የሚባል ሕዝብ እንዳይኖሩ ማድረግ ነው። ሁኔታውን በዝርዝር ለመግለጽ ግን ሰፊ አርዕስት ስለሆነ ወደዚያ አላመራም። ነገር ግን ሱዳኖች ከሌሎቹ ጋር አድርገውት የማያውቁትን በተለይ ከትግራይ ወያኔዎች ጋር 12 ዙር ሚስጥራዊ ስብሰባ ሲያካሂዱ የኖሩት ወያኔዎች ኢትዮጵያን በመንግሥትነት የማይወክሉና የኢትዮጵያ ጉዳይ ጉዳያቸው እንዳልሆነ ጠንቅቀው ስልአወቁ ነው። አለያማ በሁለቱ ብቻ በሚስጥር የሚካሄድ ምን የኢትዮጵያ ጉዳይ ይኖራል? የምዕራባውያን ሁለንተናዊ ድጋፍም ከዚህ ግንዛቤ ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህ እነሱ እነዚህን ሁሉ እያወቁ ለጥቅማቸው ሲሉ ስለአወደሷቸው ብቻ ዓለም ያወቃቸውን የአገር ጠላቶች የኢሕአዴግ መንግሥትና የኢትዮጵያ ጠ/ሚንስት እያሉ መጥራት (እኔን በግል ባይመለከተኝም) ይህን ሁሉ በሚያውቁ መንግሥታትና ሕዝቦች ሁሉ እየተሳቀብን መሆኑ የገባን አልመሰለኝም።

2. የወያኔወች መሠረታዊ ዓላማ ኢትዮጵያን በሁለመናዋ አራቁቶ ማጥፋት ስለሆነ ለወደፊት እድገቷ ከፍተኛ ድርሻ ያለውን በተፈጥሮ ሐብት የበለጸገ አካባቢ እንዳትጠቀምበት ለማድረግ ነው። ለምሳሌም Epsilon የተባለ የካናዳ የነዳጅ ማዕድን ፍለጋ ካምፓኒ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ (የሱዳን የነዳጅ ጉድጓ በተቆፈረበት አሻገር) የነዳጅ ማዕድን ፍለጋ አሰሳ አድርጎ አካባቢው ነዳጅ እንዳለበት የሚያሳዩ ምልክቶች ማግኘቱን አረጋግጧል። ወያኔ ግን ይህንን ለሀገር ዕድገት የሚጠቅም ወሳኝ ማዕድን በኢትዮጵያ ስም አውጥቶ ለኢትዮጵያ ዕድገት ከማዋል ይልቅ እጅግ በሚገርም ሁኔታ ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት ወስኗል። ደባውን ይበልጥ ግልጽ የሚያደርገው ደግሞ ለድንበር መካለሉ የሚያስፈልገውን $150, 000 የለገሰቸው የሱዳንን ነዳጅ ያወጣቸው ቻይና መሆኗ ነው። በድንበር መካለል ሰብበ ከኢትዮጵያ ወደሱዳን በሚከለለው መሬት ላይ ለእርሷ የሚጠቅም ነገር ከሌለ በስተቀር ቻይና ከሌላው ሀገር ሁሉ ቀድማ ለድንበር መካለሉ ተጨንቃ ዕርዳታ ለማድረግ ትነሳለች ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ሱዳኖች ከሁለቱ አገሮች ወሰንም አልፈው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ አዋሳኝ አውራጃወች ውስጥ ሳይቀር ምን ምን የተፈጥሮ ማዕድናት እንዳሉ አጥንተው ለእነሱ የሚበጅ አጋጣሚዎችን በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን ከ10 ዓመት በፊት ጅምሮ ሱዳን ውስጥ ሳለሁ አውቅ ነበር። ለምሳሌም ጭልጋ ውስጥ የከሰል ማዕን መኖሩን  አጣርተው ያውቃሉ።

3. ሁለቱም በስትራተጂያዊ ግባቸው ላይ ተመስርተው ወደዚያ የሚያቃርቧቸው ብዙ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስምምነቶችን እያደርጉ መቀጠላቸው ድብቅ አይደለም። ከእንዚህም አንዱ ያን አካባቢ በጋራ ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ድብቅ ስምምነት ማድረጋቸውን የሚያመላክቱ መረጃወች ይፋ እየሆኑ መምጣታቸው ነው።

3.1. ዋነኛው አመላካች መረጃ የደንበሩ ጉዳይ ድርድር የሚካሄደው መሬቱ የተከለለባቸው የአማራው፣ የቤኒሻጉሉና የጋምቤላው ተውካዮች አንዱም እንኳ ተካፋይ ባልሆኑበት በትግራይ ሕዝብ ልጆች ብቻ ማለትም በመለስ ዜናዊ፣ በረከት ስምኦንና ስዩም መስፍን ብቻ መሆኑ ነው። እንዲያውም የማይመለከተው የትግራዩ ግኘ የሆነው ጸጋየ በረሄ የጉዳዩ ዋና ተዋናይ ሆኖ ይታያል። ፕሬዚዳንት አልበሽር በሌሎቹ አካባቢወች አድርጎት የማያውቀውን በተለይ የትግራይ ሕዝብ የክብር እንግዳ ሆኖ መቀሌ ሲምነሸነሽ መሰንበቱ ለምን? የሚያሰኝ ጥያቄ የሚያስነሳ ሳይሆን ለካስ ሚስጥሩ ይኸ ነው እንዴ? የሚባልለት ሁኖዋል። ሰሞኑን ደግሞ በአንድ ሱዳንዊ ጄኔራል የሚመራ 135 ልዩ ልዩ ባለሞያዎችን ያቀፈ ቡድን 12ኛ ዙር የተባለለትን ስብሰባ በዚያችው የታላቋ ትግራይ መዲናና የልዩ እንግዶቻቸው መቀበያ በሆነችው መቀሌ ሲያካሄድ ሰንብቷል። ወያኔዎች ከኢትዮጵያዊያን ጋር ጥላቻቸው እየከረረና ጠላትነታቸው እየመረረ ከመምጣቱ በተቃራኒ ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር ቃል ኪዳን ተጋብተው ለአለሙት ግብ የሚያበቃ 12 ዙር ልዩ ስብሰባ እስከማካሄድ ሲደርሱ እኛ ግን ይኸን ሁሉ የሚያደርጉት በውስጡ ምን የቀበሩት የኢትዮጵያ ማፍረሻ ፈንጅና የቀመሙት የሕዝቧ ማጫረሻ መርዝ ቢኖር ነው? ብለን እራሳችንን በመጠየቅ ሁነኛ መልስ ያገኘንለት ሰዎች አልሆንም። ከዚህ ይልቅ እነሱ ወደዋናው ግባቸው የሚያቃርባቸውን ዝግጅት ሲያጠናቅቁ እኛ ደግም ወደቆፈሩልን መቃብር አጣድፎ የሚያወርደንና አደላድሎ የሚያስቀብረን ንክሻና የማያቃብረን ታንቲራ ስናካሂድ ኑረናል፤ አሁንም ከዚያ አልወጣንም።

3.2 አካባቢን በጋራ የማልማት ሽፋን እንደዚያ ያለውን በተፈጥሮ ሐብት የታደለ አካባቢ አዋጁ ተረቀላትና ቅድመ-ሁኔታወቿ ተሟልተውላት የተነጣይነት በዓሏን በይፋ ለማክበር ተዘጋጅታ በመጠባበቅ ላይ ለአለችው ትግራይ ሰጥቶ በመቀበል የእጅ አዙር ስምምነት ሙሉ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ የተደረገ ነው። ወያኔዎች በወረራ የያዙትን የጎንደር ክልል የበለጠ አስፋፍተው ከሱዳን ጋር በሰፊው ለማዋሰን የሚያስችላቸውን ቀጣይ እርምጃ በመውሰድ ላይ መሆናቸው ሌላው ደጋፊ መረጃ ነው።

3.3 ሰሞኑን ደግሞ ከደንበሩ ርክክብ መቃረብ ጋር ተደጋግፎ ይፋ የሆነው ተደብቆ የኖረ ሚስጥር የተሰየፉለትን ዳር ደንበር በገጸ-በረከትነት ሰጥተው ለማስመለስ ያቀዱትን የአጼ ዮሐንስን አጽም የሚመለከት ነው። እነሱ የእነሱ ብቻ አድርገው ቢያዩዋቸውም እኛ ግን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የእኛም ጭምር መሆናቸውን በጽኑዕ ስለምናምን በአጽማቸው መመለስ ከእነሱ ባላነሰ በጣም ደስተኞች ነን። እስከ አሁንም ቢሆን አንገታቸውን ቆርጠው ወስደው እንጨት ላይ በመስቀል ሰባት ዓመታት ሙሉ 360° ሲያንከራትቷቸና መዘባበቻ ሲያደርጓቸው ከኖሩት መቸም ቢሆን ጠላትነታቸው ከማይረሳ ጠላቶች ጋር እምነታቸውን አጽንተውና ፍቅራቸውን አድርተው ክብርና ትርጉም ያሳጡት እነሱ እንጅ ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን አልነበሩም፣ አይደሉምም። ሌላው ቢቀር አጼ ዮሐንስ ሠራዊታቸውን አስከትለው መተማ ድረስ ለምን ዘመቱ? ለምንስ መተማ ላይ ተሠየፉ? ለሚሉት ጥያቄወች መልስ ለማሳጣትና ሕይወት የሌለው አጽማቸውን እናስመልሳለን ብለው ህያው የክብር ሕይወት ያለውን ታሪካቸውን ያለከፈን ለመቅበር በመጣደፍ ላይ ያሉት እነሱ ናቸው። ለገጸ-በረከት የመሰጠቱም ማረጋገጫ የሚሆነው ይኸው ነው። አለያማ ሱዳኖች የጀግንነታቸው መግለጫ አድርገው ለ120 ዓመታት ሲፎክሩ የኖሩበትን አጽም ከሙዝየማቸው አውጥተው በነጻ ይሰጣሉ ማለት ሱዳኖች **የሱዳንነታቸውን** ግብር ለውጠዋል እንደማለት የሚቆጠር በመሆኑ ነው።

4. የኢትዮጵያን ሩሂ (ስልሞ) አንቀው መተንፈሻና መላወሻ በማሳጣት የእነሱን ወለል አድርገው ለመክፈት ተስፋቸውን ጥለውበት የነበረው አሰብ ተስፋ ያስቆረጣቸው ሀገራዊ ተስፋ የለሾች ያን የሚተካ የየብስና የባህር በር መገናኛ በሱዳን በኩል ትግራይ እንዲኖራት ለማድረግ በማካሄድ ላይ ያሉት ቅድመ-ዝግጅት ሁሉ የዓላማና ግባቸውን ተደጋግፎ መቀጠል የሚያረጋግጥ ነው። አስመሳዩ ዶክተር አረጋዊ ግን እነዚህን ሁሉ በማስመሰያ ምክንያት ለመከላከል ጥረዋል። የሰው ልጅ አንድም በተፈጥሮው እራሱን ማየትና መግዛት የሚችልበት ህሊና ከሌለው፣ አልያም ገሐድ እውነታዎች የማይገዙት ከሆነ ከቅርጽ ባልፈ የተሟላ የሰውነት ሥነ-ባህሪይ አለው ለማለት ይከብዳል። ዶክተሩ መስለው ብቻም ሳይሆን ሆነው የሚታዩት የዚህ ዓይነት ሰው ነው። ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ያን አካባቢ በሚመለከት ምን እያሉ ለማስተባበል እንደሞከሩ ቃል በቃል እየጠቀስኩ ለማብራራት እሞክራለሁ።

5. በጽሑፋቸው ገጽ 7 "ለሱዳን ተሰጠ የተባለው መሬትም ቢሆን የትግራይ ሕዝብ እንደማንም ኢትዮጵያዊ ለዳር ድንበሩ ቀናኢ በመሆኑ መስዋእትነት እንደሚከፍል መጠራጠረዎ ያሳዝናል። የትግራይ ሕዝብ ላገሩ ዳር ደንበር መከበር መስዋዕትነትን ሲከፍል የኖረና በተግባር ያስመሰከረ በመሆኑ የጄኔራል ኃይሌ መለሰን ሰርቲፊኬት አያስፈልገውም።...ለመሆኑ ሌላው ኢትዮጵያዊ ወደ ግንባር ከቶ የትግራይ ህዝብ ባለመሳተፉ ነው ሱዳን መሬታችንን የሚወስደው ወይስ ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን በመጨበጡ የትግራይ ህዝብ ሥልጣን ጨብጧልና ከሌላው የበለጠ ሓላፊነት አለበት ነው የሚሉን?.. ታዲያ በዚህ ሁኔታ የትግራ ህዝብ ምን ያድርግ ነው የሚሉት?.. እንደሚያውቁት ምንም መረጃ ላይደርሰው ስለሚችል ለውንጀላ ከመሽቀዳደም ረጋ ብሎ ጊዜ ወስዶ አጥንቶና አስተውሎ ፍርድ መስጠት ከመሳሳት ያድናልና ረጋ ብለው ቢያመዛዝኑ መልካም ነው።" የሚል "ምክራቸውን" ለግሰውኛል። ነገር ግን አባባላቸው



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ትዝብትን የማይፈሩት ዶ/ር የበለጠ ትዝብትን እንዲላበሱ የሚያደርግ እንጅ ትምህርት ሰጭ ሆነው የሚያገለግሉ አይደሉም። የተወሰኑትን መለስ ብየ ልጥቀሳቸው።

5.1 በመጀመሪያ የምጠቅሳቸው እኔን ልምከርህ ብለው የተናገሯቸውን ቃሎች ነው። በመሠረቱ ትምህርት ከእብድም ከጭምትም ይገኛል እንደሚባለው እንደ እሳቸው ካለ ዶክተር ተብየ ቀርቶ ከማንም ቢሆን የሚጠቅመኝ እስከሆነ ድረስ በደስታ ተቀብየ ለጠቀም ዝግጁ ነኝ። ነገር ግን ኢትዮጵያ የምትባል አገር አልነበረችም ከማለት ጀምሮ አለች የምትባለውንም ብትሆን ጨርሰን ማጥፋትና ሕዝቧን እርስ በርሱ ማጫረስ አልብን ብለው ሲዘምቱና ሲያዝምቱ የኖሩት የማሌሊት መስራችና መሪ "ረጋ ብሎ ጊዜ ወስዶ አጥንቶና አስተውሎ ፍርድ መስጠት ከመሳሳት ያድናል" ብለው በእውን መናገር የሚገባቸው ሰው ናቸውን? እሳቸውም ሆኑ የዓላማና የግብር አጋሮቻቸው እንዲህ ያለ ተፈጥሮአዊ ታድሎ ወይም ትምህርትና ልምድ ያነጸው ህሊና ቢኖራቸውማ ኖሮ መጀመሪያውኑ ምን ችግር ነበር። ስለዚህ ቃሉን በመናገራቸው ብቻ ብቃት ያለው መካሪና ዘካሪ መስለው ለመታየት እንኳ ቢሆን በቅድሚያ ማስተማር የነበረባቸው እራሳቸውንና የግብር አጋሮቻቸውን ነበር። እንደኔ አስተያየት ግን ትላንት ሲጀምሩ ቀርቶ ዛሬ እንኳ መጨረሻቸው ሲቃረብ እራሳቸውን አስተምረው ያልለወጡ የዕድሜ ልክ የመንደር አምባሳደር ብሔራዊ አድማስ ያላቸውን ኢትዮጵያዊያን ለማስተማር የሚችሉበት የሞያም ሆነ የሞራል ብቃት ይኖራቸዋል የሚል ግምት የለኝም።

5.2 ሌላው ለዳር ደንበሩ ቀናኢና መስዋዕትነት ከፋይ በሆነው የትግራይ ሕዝብ ላይ ለምን ጥርጣሬ አሳደርክ ብለው ሐዘናቸውን መግለጻቸው ነው። ሁሉንም በመሰላቸው መተርጎም ልምድ ሆኖባቸው እንጅ እኔ ግን የገለጽኩት ከመጠራጠርም አልፌ ከ20 ዓመታት በላይ በገሐድ ሲያካሂድ በኖረው ኢትዮጵያዊ ሐላፊነት በጎደለው ድርጊት ላይ ተመስርቶ በመሆኑ የግምገማ አስተያየቴን እንድጠራጠረው የሚያደርግ አንድም ነጥብ የለም። ይልቅየ ከማሳዘንም አልፎ እስከ መጨረሻው ድረስ ሲያሳፍርና አንገት ሲያስደፋ የሚኖረው የታሪክ ጠባሳ ክህደትን እንደጽድቅ በመቁጠር ዘሎ ገብቶ የፈጸሙት ሁለንተናዊ ውድመት የማያዛልቅ ሆኖ ሲገኝና ማጠፊያው ሲያጥር የሚሞከረረው ሁለተኛ ዙር የዕውር ድንብስ ጉዞ ነው። **በመጀመሪያ ደረጃ የምንነጋገረው በትግራይ ሕዝብ ምክንያት ስለመጣው የወቅቱ ችግር እንጅ ስለዘመናት ታሪክ አይደለም።** ወደዚያም ካመራን እኔም ሆንኩ ሌሎቹ ኢትዮጵያን የትግራይን ሕዝብ ከኢትዮጵያ የዘመናት ታሪክ ማህደር ለይተን ያሳየንበት ቦታና የገለጽንበት ቃል ፈጽሞ የለም። እንዲያውም በተቃራኒው የትግራይን ሕዝብ ታሪክ አልባ ያደረጉት በዘረኝነት በሽታ ተለክፈው እንደ እንቁላል የገሙት የራሱ ልጆች ናቸው። ለዚህ አባባል ብዙ መረጃወችን መጥቀስ ቢቻልም በአጭሩ ግን ዮሐንስንና አሉላን ከእነ ታሪካቸው ክዶ የእነሙሶሎኒ ቅጥረኛ የሆነውን መለስ ዜናዊን አምላኪ የሆነው የትግራይ ሕዝብ ለዳር ደንበሩ ቀናዔ ነው ማለት ቁንቁን እንደበላው እንጨት ውስጡ ባዶ የሆነ ከንቱ ጨኸት እንጅ ህሊና ሊቀበለው የሚችል አሳማኝ እውነት ፈጽሞ የለውም። የእናት አገሩን ጥፋት ከ20 ዓመታት በላይ ሲያስተናግድና በድምቀት ሲያከብር የኖረበትን ድርጊት ብቻ መጥቀስ በቂ ማረጋገጫ ይመስለኛል። ለጀግኖች ልጆቹ ያቆማቸው



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ሐውልቶችና የሰጣቸው ሹመትና ሽልማቶች ሁሉ ለምን ዓላማ ዘምተውና የማንን ውድ ልጆች በየበረሐው አርግፈው ነው የሚያሰኙ ጥያቄዎች በተነሱ ቁጥር በትግራይ ሕዝብ ላይ እየመሰከሩ የተጠያቂነት እዳውን ከሚያበዙበት በስተቀር የሚቀንሱለት አይደሉም። በእርግጥ የአሁኑ የትግራይ ሕዝብ እንደ ትላንት አባቶቹ ለዳር ደንበሩ ቀናዔና መስዋዕትነት ከፋይ ቢሆንማ ኖሮ ትግሉን መጀመር የነበረበት ዮሐንስና አሉላ ቅኝ ገዥወች ናቸው ተብለው ሲፈረጁ፣ እነሱ ያጸኑት የብሔራዊ አንድነት መሠረት ሲናድና አስከብረውት የኖሩት የባህር በር ሲዘጋ ነበር። እነዚህን ሁሉ እንደ ከፍተኛ ድልና ክብር ቆጥሮ እያከበረ ሲፎክርና ሲጨፍር የኖረን የትግራይ ሕዝብ ለዳር ደንበሩ ቀናኤ ነው ማለት ግን ትርጉም የለሽ ከንቱ አምልኮትና ወቅቱ ያለፈበት መፈክር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ከወቅቱ ችግር ጋር ባይገናኝም እንደማቅና ጨርቅ አቀራኝተው ላቀረቡት ነጥብ መልስ ሰጥቸበት ለማለፍ ስል አዎ! የትግራይ ልጆች በእኔ እዝ ይመራ በነበረው 69ኝ ሚሊሺያ ብርጌድ ሥር በምስራቅ ጦር ግንባር ተሰልፈው በጀግንነት ተዋግተዋል፣ የተደፈረ ብሔራዊ ወሰናቸውንም አስከብረዋል። የወቅቱ ጥያቄ ግን ጀግኖቹ ስለአስከበሩት የምስራቅ ጦር ግንባር ሳይሆን ከሐዲዎቹ እነአረጋዊ በረሄ አሳልፈው ስለሸጡት መሬትና ስለአናጉት ሀገራዊ አንድነት መሆኑን ሊረዱት ይገባል።

5.3 ሌላው የትግራይ ሕዝብ ስለዚያ አካባቢ መሬት መወሰድ መረጃው አልደረሰውም ማለታቸው ነው። አባባላቸው በአለው አንድምታ ከተተረጎመ የትግራይ ሕዝብ ስለአገሩ ወቅታዊ ሁኔታዎች የሚያዳምጥበት ጀሮ፣ መከታተል የሚችልበት ንቃትና የሚያመዛዝንበት ህሊና የለውም እንደማለት የሚቆጠር ጸያፍ አባባል ነው። እኔ ግን የትግራይን ሕዝብ በዚህ መልክ አላየውም። ለሱዳን ስለተሰጠው መሬትም ቢሆን ከሌሎቹ በተለይ በይፋ የሚነገረውን ቀርቶ ልጆቹ በሚስጥር የያዟቸውን ጉዳዩች ሁሉ ጠንቅቆ እንደሚያውቅ መረጃው አለኝ። ማረጋገጫ መረጃዎቸም፣

- መሬቱን ከልለው ለመስጠት የመከሩና የዘከሩ፣ በሚስጥር ተደራድረው ለመስጠት የወሰኑ እሱ ነጻ ያወጡኝ ናቸው ብሎ የሚመካባቸው ልጆቹ ናቸው፣
- የአካባቢውን ነዋሪ ሕዝብ እያፈናቀለና የተቃዎሙትን እየገደለ መሬቱን ለሱዳኖች በማስረከብ ላይ ያለው የትግራይ ሕዝብ አደራጅቶ ያዘመተው አጋዚ የተባለው ጦር ነው፣
- በርካታ የትግራይ ሕዝብ ተከዜን ተሻግሮ በወረራ በያዘው መሬት ላይ መስፈር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ለሱዳኖች ከልለው እስከሰጡት ወሰን ድረስ ተደላድሎ እየኖረ ነው። የወያኔዎች አምባሳደር ለትግራይ ሕዝብ መረጃው አልደርሰውም ሲሉ እነዚህ ሁሉ በየፈርጁ ያዘመታቸው ልጆቹ አንድም አልነገሩቱም፣ አልያም የት እንደሰፈሩና ወደየት እንደዘመቱ አያውቅም ለማለት ፈልገው እንደሆነ ለእኔ ግልጽ አይደለም። ሌላው ቢቀር ፕሬዚዳንት አልበሽርንና በጄኔራሉ የተመሩትን ሉካን በመቀሌ ተቀብሎ ሲያስተናግድ የሰነበተው የትግራይ ሕዝብ ያላወቀው ሚስጥር ነው ብሎ እንደመናገር የሚቆጠር ነው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

5.4 “የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ደም የተከፈልበትን የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መሬቶች በህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች ለሻቢያ ሲቸሩ ሲውጠነጥን በዓይኑ ሥር እየተፈጸመ ያለ ጉድ በመሆኑ እንቢ አልሰጥም ብሎ ግብግብ ፈጥሮ እንደነበር የሚታወስ ነው።” ይሉናል። ኢትዮጵያዊ ራዕይ የሌላቸው መንደርተኛ ዶ/ር ኢትዮጵያዊ ደም የተከፈለበት የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መሬቶች የሚሉን የትግራይ ክልል ስለሆነ ብቻ ነው። አለያማ ትላንት በቀይ ኮከብ ዘመቻና በትግራይ ክልል በራሳቸው አዝማችነት ምን ሲያደርጉ እንደኖሩ ህሊናቸው እያወቀ እንዲህ ባላሉን ነበር። የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ደም የተከፈለባቸውን የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መሬቶች ላለመስጠት ግብግብ ይገጥማል ከተባለም መግጠም የነበረበትና ያለበት ለባድሜ ብቻ ሳይሆን ለኤርትራም፣ ለአሰብም፣ ለአገሪቱ ምዕራባዊ የአስተዳደር ክልልም ጭምር መሆን ነበረበት። የአንድነት መሠረትና የስልጣኔ ምንጭ ነው እየተባለ ሲነገርለት የኖረው ሕዝብ በራሱ ልጆች አይደለህም፣ ከ100 ዓመት በፊትም እንዲህ ያለ ታሪክ የለህም ተብሎ ሲካድ ነበር እንቢታው መጀመር የነበረበት። አፄ ዮሐንስና ራስ አሉላ ከነሠራዊታቸው ኤርትራ ውስጥ በዶጋሌ፣ በጉንድት፣ በጉራዕ፣ በከረንና ምጽዋ ወዘተ፣ ጎንደር ውስጥ ደግሞ በመተማ ጦርነቶች ያፈሰሱት ደምና የከፈሉት መስዋዕትነት ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት የተከፈለ ኢትዮጵያዊ ደምና ያለፈ ህይዎት አይደለም ተብሎ ሲካድ ነበር ግብግቡ መጀመር የነበረበት። ባለፉት 30 ዓመታት ትግራይና ኤርትራ ውስጥ ከጣምራ ከሐዲዎች ጋር በተካሄደ ቀጣይ ጦርነት የኢትዮጵያ ሠራዊት ያፈሰሰው ደም፣ ያረገፈው አጽምና የከፈለው መስዋዕትነት ሁሉ ተመሳሳይ ትርጉም ያለው፣ ተመሳሳይ ጥያቄ አዝሎ የሚኖርና ተመሳሳይ ፍርድ የሚጥብቅ ንጹህ የአቤል ደም መሆኑን የወያኔዎች ዶ/ር የተረዱት አልመሰለኝም። ሌላው ቢቀር መሳሪያ ታጥቆ በዘመተው ብቻም ሳይሆን ጀሌው ሕዝብ በጢስ ከቶ በጦር እየወጋ፣ በገጀራ እየቆረጠና በመጥረቢያ እየፈለጠ፣ ሴቶቹ ደግሞ የእሳት እረመጥና የበርበሬ ዱቄት በላዩ ላይ እየረጩ በርብርቦሽ የፈጁት የኢትዮጵያ ሠራዊትና የመሪዎቹ የእነ ጄ/ል አዲስ አግላቸው፣ የእነ ጄ/ል ኃይሉ ከበደ፣ የእነ ጄ/ል ለገሰ አበጀ  አጽም ሲወጋና ሲያዋጋ የሚኖር ባለብዙ መዘዝ እዳ እንጅ የሽሬ አረም አልብሶት የሚቀር ብናኝ አፈር መስሎ ታይቷቸው እንደሁ በእጅጉ ተሳስተዋል።

ይኸን ሁሉ ግፍና በደል ሲያካሂዱ የሚኖሩትን ልጆቹን አቅፎ ደግፎ የያዘና የማጥፊያ መሳሪያ ሆኖ ሲያገለግል የኖረው የትግራይ ሕዝብ ትላንት ባድሜን ሊሰጡበት ሲሉ በግብግብም ይባል በቤተሰባዊ ድርድር ቢያስቀርም ዛሬ ደግሞ ከባድሜ በብዙ መልኩ የበለጠና የሰፋ መሬት (ከጎንደር እስከ ጋምቤላ) አሳልፈው እየሰጡ ናቸው። ልዩነቱ ግን የትግራይ ሕዝብ ባድሜ ላይ አሳይቷል የተባለውን ግብግብ ለዚህና ለሌሎቹም አካባቢዎች ለማድረግ አለመፈለጉ ብቻም ሳይሆን እንዲያውም በተቃራኒው ተላልፈው እንዲሰጡ ከፍተኛ ድጋፍ መስጠቱ ነው። እኔ ስለተናገርኩት ብቻ ክደውት የነበረውን የትግራይን ሕዝብ የማድረግ ችሎታ ዶ/ሩ በራሳቸው አባባል ስላረጋገጡልን ግን በዚህ አጋጣሚ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። የትግራይን ሕዝብ ከማያመልጥበት ባለብዙ መልክ የተጠያቂነት እዳ ነፃ ለማድረግ ሲሉ እነዚህን ሁሉ እንደባድሜ በዓይኑ ሥር ካልሆኑ በስተቀር ሊያያቸውና በወሬ ደረጃም ሊሰማቸው አይችልም ማለታቸው ግን የትዝብት ልብሳቸውን



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ከሚያረዝምላቸው በስተቀር ሐቁ ግን አውቆ የተደበቀ ቢጠሩት አቤት አይልም መሆኑ ሊያጥራጥረን አይገባም።

እንዲያውም ክብርና ውርድት ከምን ጋር ተያይዘው እንደሚመጡ በውል ለይቶ ማወቅ ያልቻሉት ዶ/ር የትግራይን ሕዝብ በአክብሮት መግለጼን አዛብተው በመተርጎም ከእኔ ሰርቲፊኬት እንደማያስፈልገው በምጸት እስከመናገር አድርሷቸዋል። እኔ እንደሚገባኝ ሰርቲፊኬት ብቻም ሳይሆን ከዚያም በላይ የሆኑ ሹመትና ሽልማቶች የሚሰጡት ዜግነታቸውን ክደው ወይም ግዴታቸውን ዘንግተው በእናት አገራቸው ላይ ለዘመቱ ሳይሆን በማንኛውም የግንባታ መስክ ወይም አገርን የመከላከል ዘመቻ ተሰልፈው ውጤታማ ሥራ ለሠሩ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ሕዝብ ይመስለኛል። ከዚህ አንፃር ለራሴ መመስከሬ ለህሊናየ ቢከብደኝም ዶ/ሩ ለተናገሩት የምጸት ቃል ሐቁን ለመግለጽ ያህል መስፈርቱን ወይም ብቃቱን አሟልተው ለሚገኙ ሁሉ ሰርቲፊኬት ለመስጠት ብቃቱ ሞልቶ የተረፈኝና በዚህ ለደኸዩም መመጽዎት የምችል መሆኔን ላረጋግጥላቸው እወዳለሁ። ምክንያቱም ኃይሌ መለሰ ማለት ለእናት አገሩ ሉዐላዊነትና ለሕዝቧ ነፃነትና ክብር አካሉን ደጋግሞ በጥይት ያሳረሰና ንጹህ ደሙን ያፈሰሰ፣ በእምነቱ የጸና፣ በሞራሉ የኮራ፣ በተግባሩ የበለጸገ፣ በሥነ ምግባሩ ንጹህ ኢትዮጵያዊ ጄኔራል መኮንን በመሆኑ ነው። ከዚህም አልፌ ብዙ ማለት የምችላቸው ነጥቦች ቢኖሩኝም የሞያም ሆኑ የትግል አጋሮቹን ሞራል ሊነካ ይችላል በሚል ስጋት ከማድረግ ተቆጥቤያለሁ። ይህን እናስተባብላለን የሚሉ ካሉም አለሁላቸው። ይህን ስል ግን ሰው እንደመሆኔ መጠን ስህተት ሳልሠራ የኖርኩ ፍጹም ነኝ ማለቴ አይደለም። እንደማንኛውም ሰው ሥሠራ የተሳሳትኳቸው ብዙ ስህተቶች እንደሚኖሩብኝ አምናለሁ። ነገር ግን መቼም ይሁን የት? በማንም ላይ ይሁን ምን? ከተወለድኩባቸውና ከምትካቸው ትውልዶቹም አልፎ አገሬንና ወገኔን የሚያኮራና የሚያስከብር እንጅ የሚጎዳም ሆነ የሚያሳፍር ድርጊት እንዳልፈጸምኩ በእርግጠኝነት እናገራለሁ።

በእርግጥ እንዲህ ያለው የኢትዮጵያዊ ሰውነት መለኪያ አውጭ እንደሚባለው አውሬ ይመስል የጀግኖች አባቶቻቸውን የክብር መቃብር እየፈነቀሉ ማርከሰንና እነሱ ያጸኑትን የአንድነት መሠረት ማፍረስን እንደ ጀግንነት ለሚቆጥሩ ከሐዲዎች ህሊና የሚከብድ ይመስለኛል። እኔን ሰርቲፊኬት መስጠት አትችልም ያሉኝ ዶ/ር ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ይህን አድርጌያለሁ ብለው ሰርቲፊኬት የሚያሰጣቸው ቀርቶ የዜገነት መታወቂያ ካርድ እንኳ የማግኘት እድል ያላቸው አይመስለኝም። መቼም ስደት መቁረጭት ሆኖ በቃላት ደርጃ ሁሉንም ስለሚያስተካክል እንጅ የነገሮች መልክ ተለውጥው ወደ አገር የመግባት ጉዞ ቢጀመር ዶ/ር አረጋዊን ጨምሮ ሌሎቹም ወያኔዎች በሥራቸው እምነትና በሞራላቸው ብቃት ኖሮዋቸው አብረውን እንደማይገቡ እርግጠኛ ነኝ። ምክንያቱም በክፍል ሁለት ጽሑፌ እንደገለጽኩት የእነሱ የማስመሰያ ኢትዮጵያዊ ተቆርቋሪነት አስቀድሞ የተገሠሠ በመሆኑ ነው። በእርግጥ ንስሐ ገብቶና ሐጢአትን በግልጽ ተናዞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምህረት መለመን ስጋዊ ክብረ ንጽህናን ባይመልስም መንፈሳዊ ድንግልናን ማስገኘቱ አያጠያይቅም። ወያኔዎች ግን በዚህ የተበደሉ እንጅ ይህን ለማድረግ የታደሉ ባለመሆናቸው የእነሱ ኢትዮጵያዊ ድንግልና



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የመመለስ እድሉ ያከተመለት ይመስላል። በመሠረቱም ዕምነት በአንጀት ውስጥ በቅሎ ሲለመልምና በህሊና ተቀርጾ ሲነበብ የሚኖር የእድሜ ልክ አምልኮት እንጅ እንደብፌ ምግብ ካዩት ሁሉ እየቀላወጡ በተነፉ ቁጥር የሚደነክሩበት የዓለማዊ ህይወት ድብብቆሽ ጨዋታ ባለመሆኑ ነው። ስለዚህ የትግራይ ሕዝብ ከእኔ ሰርቲፊኬት አገኘ ማለት ዶ/ር አርጋዊና የመሠረቱት ድርጅት አባሎች ያሳጡትን ኢትዮጵያዊነት መልሶ እንዳገኘ የሚቆጠር ነው ብየ ባጠቃልለው አጋንኘ ያቀረብኩት አይመስለኝም። ይልቅየ አጠያያቂው ጥያቄ በእናት አገሩ ላይ ለዘመቱ ልጆቹ ሁለንተናዊ ድጋፍ እየሰጠ አብሮ ሲዘምት የኖረው የትግራይ ሕዝብ ከኢትዮጵያዊው ጄኔራል መኮነን ሰርቲፊኬት ለመቀበል የሚያበቃው ተግባራዊ ማረጋገጫና የሞራል ብቃት አለው ወይ? የሚለው መሆን አለበት። ስለሆነም በከሐዲ ልጆቹ የቱንም ያህል ምክንያት ቢደረደርና ቃላት ቢከመር፣ እሱም እነዚህ ሁሉ መደርጋቸውን አላውቅም፣ ሲወራም አልሰማሁም ብሎ ቢያስተባብል ከተጠያቂነት እዳ ማምለጥ የሚችልበት እድል እንደሌለው በውል ሊታወቅ ይገባል።

6. ዶ/ሩ ከባድ ጥያቄ አድርገው ያቀረቡልኝ “ለመሆኑ ሌላው ኢትዮጵያዊ ወደ ግንባር ከቶ የትግራይ ህዝብ ባለመሳተፉ ነው ሱዳን መሬታችንን የሚወስደው ወይስ ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን በመጨበጡ የትግራይ ህዝብ ሥልጣን ጨብጧልና ከሌላው የበለጠ ሓላፊነት አለበት ነው የሚሉት?..ታዲያ በዚህ ሁኔታ የትግራይ ህዝብ ምን ያድርግ ነው የሚሉት? የሚሉ ሁለት ጥያቄዎች ናቸው። ለእኔ ግን በጥያቄዎቹ መሠርት የትግራይ ሕዝብ መወጣት የሚገባውን ኢትዮጵያዊ ግዴት ያለምንም አሻሚ ቃልና ዲፕሎማሲያዊ ቋንቋ በድጋሜ ለመንገር በጣም የሚያመቹ አጋዥ ጥያቄዎች ሆነው አግቻቸዋለሁ።

6.1. ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ግንባር መክተት የሌላውን ወቅትና ግንባር ታሪክ አቆይቸ በጣዕር ተይዘው ሲጯጯሁ በነበሩበት ወቅት ከቶ እሳቸው ያልካዱትን ኢትዮጵያዊ ደም እንደጎርፍ ያፈሰሰበትን የባድሜን ጦርነት ታሪክ መለስ ብለው ቢያገናዝቡ መልስ ይሰጣቸዋል ብየ አምናለሁ። ለእነሱ ክልል ዘምቶ ማስከበር የቻለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለብሔራዊ ዳር ደንበሩ አይከትም የሚል ጥርጣሬ ካላቸው ግን ተሳስተዋል። ለሱዳን ስለተሰጠው አካባቢ ግን የሱዳን ጦር አስቀድሞም የሚያውቃቸው የአካባቢ ጀግኖች ከበቂ በላይ በመሆናቸው የሌላውን ኢትዮጵያውዊ መክተት አልጠየቀም። የአካባቢውም ሕዝብ እንደ ወያኔዎች የትግራይን ሕዝብ ድረስልን ብሎ አልተማጸነም። ያልጠየቀው በአንድ በኩል እራሱን ሊያውል በሚያስችል ሞራላዊ ጉልበቱ ለመወጣት ስለፈለገ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለቀባሪ አያረዱም እንደሚባለው ድርጊቱን ማን እንዳደረገው ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ነው። የኔም ጽሑፍ ቢሆን ዶ/ሩ በሰጡት ትርጉም የሚነበብ መልዕክት የለውም። ያልኩት ቢኖር እንደ ባድሜ ይኸም የእኔ ነው የሚል ከሆነ የኢትዮጵያዊነት ግዴታውን ሊወጣ ይገባል የሚል ነው። ትክክልም ነኝ። ኢትዮጵያዊ ግዴታውን ሊወጣ ይገባል ስል ግን ልጆቹ አሳልፈው ለመስጠት የከለሉትን መሬት የኛም ጭምር ስለሆነ ለምን ይሰጣል ብሎ መጠየቅ አለበት ማለት እንጅ ከእኛ ጎን ተሰልፈህ ልጆችህን ውጋልን ማለት አይደለም። እንደማያደርገው እያውቅሁ እንዲህ ያለውን ጥያቄ መጀመሪያውንም አልጠይቅም።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ምክንያቱም እንደዚያ የሚያደርግ ቢሆንማ ኖሮ አስቀድሞ ማድረግ የሚገባው ብዙ ነገሮች እንደነበሩ ስለማውቅ ነው።

6.2. ሌላው እውነታ ሱዳኖች የዚያን አካባቢ ሕዝብ ማንነት ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ብቻቸውን መጥታችሁ ተረከቡ ቢባሉ እንኳ ወሰኑን አያልፏትም። ምክንያቱም በእነ አባደፋር አዳነ መኮንን አዝማችነት የዘመተው ኃይል እያሳደደ እንደመነጠራቸውና በሥርዓት ለመሸሽ እንኳ እድል እንዳልሰጣቸው ስለሚያውቁ ነው። ከደርግ በፊት ተገንጣይን ብለው የዘመቱ ጀግኖችም ወያኔዎችን ምን ያህል እያራወጡ ይመነጥሯቸው እንደነበር ያልሻረው ቁስላቸው ይመሰክርባቸውል። ዛሬም ቢሆን የአባቶቻቸውን ታሪክና ወኔ የወረሱት ጀግኖች ልጆቻቸው በሱዳን ጦር ከማሳቸው ላይ ታፈነው የተወሰዱ ወገኖቻቸውን ለማስመለስ ሲሉ አንድ አውቶብስ ሙሉ ሰወች እንደጫኑ ማርከው ሲወስዱ ከሱዳኖች የመከታቸው ቀርቶ የሞከራቸው እንኳ አልነበረም። የጀግኖቹን ምርኮ ያስመለሰው የአጋዚ ጦር በተዋጊ ሄሊኮፕተር ታግዞ ዘምቶ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠንቅቆ ያውቃል። ከሱዳን ጦር ጋር ግንባር በመፍጠር ነዋሪውን ሕዝብ እያስገደደ የሚያፈናቅልና ንብረታቸውን የሚዘርፍ፣ ዳር ደንበራችን መደፈር የለበትም ብለው የተሰለፉትን ደግሞ እያሳደደ በመበቀል መሬቱን እየከለለ በማስረከብ ላይ ያለው ይኸው የትግራይ ሕዝብ ጦር ነው። ስለዚህ የሕዝቡ ጥያቄ ሰላም የነሱንና መኖሪያ አገር ያሳጡንን ልጆችህን አስተወን የሚል ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ ጥያቄ አላቀረበም፣ የለውምም። ከሱዳኖች ጋር ግንባር በመፍጠር ኢትዮጵያውያንን ማህል አስገብቶ ለመጨፍጨፍ መዝመት ግን መቸውንም ቢሆን ከትግራይ ሕዝብ ራስ ላይ ሊወርድ የማይችልና ለልጅ ልጅ ሲተላለፍ የሚኖር ከባድ የደም እዳና ብዙ መዘዝ ያለበት ችግር መሆኑ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል። በእሱ ስም በትውልድ ሲያጠያይቅና በታሪክ ሲያፈራርድ የሚኖር ክህደትና ውድመት እያደረሱ የደም እዳውና አገር የማጥፋት ወንጀሉ የትግራይን ሕዝብ አይመለከተውም ማለት ግን በግፍ የፈሰሰ ቀርቶ የንጹህ ደም ጠብታ እንኳ የምታስከትለውን መዘዝ አስቀድሞ ያለማወቅ ዘረኝነት የበከለው ድንቁርና ነው።

6.3. "..ወይስ ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን በመጨበጡ የትግራይ ህዝብ ሥልጣን ጨብጧልና ከሌላው የበለጠ ሓላፊነት አለበት ነው የሚሉን?" ያሉትን ጥያቄ ልመልስላቸው። አዎ! መጠርጠሩስ! በዘረኝነት የታወሩት ዶ/ር ያልገባቸው ቢኖር ንጉሣቸው መለስ ዜናዊና የአገር ማጥፊያ ድርጅታቸው እንደ አብርሐም (በተለምዶ እንደሚነገረው) 500 ዓመት አይኖሩም። የፈጸሙት ሁለንተናዊ ወንጀል ግን ከ500 ዓመታትም በላይ የትግራይን ሕዝብ ሲይጎብጥ የሚኖር መሆኑን ነው። ባለፈው ጽሑፌ ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል ያልኩትም ዛሬ ብቸኛ ተጠቃሚና አጥቂ የሆነው የትግራይ ሕዝብ ነገ ደግሞ ብቸኛ የተከማቸ እዳ ከፋይ እንዲሆን ይገደዳል ማለቴ ነበር። ምክንያቱም በመጀመሪያ ኢህአዴግ የወያኔዎች የክህደት አምልኮት ማድመቂያ ቃል እንጅ በዚህ ስም የሚጠራ መንግሥት በኢትዮጵያ የለም። የማይቀረው የተጠያቂነት መርግ እየተንከባለለ ሲመጣ ይጋራልናል ተብሎ ታስቦ እንደሆን ከንቱ ምኞት ይመስለኛል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ላይ ነግሦ ያለው የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ብቻ ነው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ስለዚህ የትግራይን ሕዝብ ምንም ከሌለበት ሕዝብ ጋር በማነጻጸር የበለጠ ሐላፊነት አለበት ወይ? የሚያሰኝ ጥያቄ የሚያስነሳ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ሐላፊነትና ተጠያቂነት ያለበት መሆኑን ሊያውቁ ይገባል። ወያኔዎች በዚህች ታሪካዊት አገርና ብዙ ችግሮች በሚፈራረቁበት ሕዝብ ላይ እንደፈለጉ ለማድረግ የቻሉበትን ሥልጣን ያስጨበጣቸው የትግራይ ሕዝብ ነው። በዙሪያ ገባቸው ዘብ ቁሞ የሚጠብቃቸው፣ ሁለንተናዊ ድጋፍ እየሰጠ ያጠናከራቸው፣ የማጥፊያም ሆነ የመግደያ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግላቸውም የትግራይ ሕዝብ ነው። የእሳቸውን አባባል ብዋስ የትግራይ ሕዝብ ለትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት የደጀን ኃይል መሆኑን መልሰው ካልካዱን በሰተቀር በራሳቸው አንደበት አረጋግጠውልናል። ስለዚህ ውሁድ ሁነው የያዙትን ሥልጣነ መንግሥትና ተደጋግፌው ሲፈጽሙ የኖሩትን ድርጊ ለፖለቲካ ሸሬታ ሲባል ከሁለት ከፍሎ ማየትና ህወሓት/ኢህአዴግ እያሉ መጥራት እራስን ከማታለል ባለፈ የቁርጡ ቀን የሚያስገኘው ፋይዳም ሆነ የሚታደገው አንዳችም ነገር የለም። በእርግጥ እስከዚያው ድረስ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስትር እየተባለ እንደሚጠራው ሁሉ የትግራይም ሕዝብ የለበትም እያሉ ማዝገም ይቻላል። ነገር ግን በወያኔዎችና በትግራይ ሕዝብ መካከል ውሁድ የሆነ ግንኙነት የላቸውም ማለት ወያኔዎች የትግራይ ሕዝብ ልጆች አይደሉም ብሎ እንደመካድ ስለሚቆጠር ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም።

በመሠርቱ መንግሥት ሲባል በወል መጠሪያነቱም ሆነ (ወያኔዎች በዚህ መስፈርት ውስጥ ባይገቡም) በፖለቲካና መደባዊ ባህሪዩ ከታየ ሰፌ ትንተናን ስለሚጠይቅ ወደዚያ አላመራም። አስምሬበት ለመግለጽ የምፈልገው ግን የትግራይ ሕዝብና ወያኔዎች የሥልጣን ተጋሪዎች ናቸው ስል ካላቸው ባለብዙ መልክ መሰተጋብራዊ ግንኙነት አኳያ እንጅ በሥልጣን ላይ የነበሩና ያሉ መንግሥታት ሁሉ የፈጸሙትና የሚፈጽሙት ግፍና በደሎች ሁሉ ሕዝብን ያስጠይቃሉ ለማለት አይደለም። ለምሳሌም ወያኔዎች የከረፋ ዘረኝነታቸው ጠረን መለወጫና የተሰበረ ስማቸው መጠገኛ ወጌሻ አድርገው የሚገለገሉበትን የደርግን መንግሥት በዋቢነት ልጥቀስ። የደርግ መንግሥት ወንጀል (አገር ጠበቅና ሕዝብ ጠቀም ጎኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) የአገሪቱን ሕዝብ በጎሳና ሐይማኖት ሳይለይ በመበደሉ እንጅ ለአንዱ ብሔረሰብ ብቻ ወግኖ ሌሎቹን ብሔረሰቦች ለማጥፋት ያቀነባበረው ሴራና ያካሄደው ዘመቻ የለም። የተለየ ተጠቃሚ ለማድረግ ለይቶ ያለማው ልማትና ተጠቃሚ ታደረገው ብሔረሰብም የለም። ስለሆነም እንዲህ ያለው ብሔረሰብ ከደርግ መንግሥት ጋር የሥልጣን ተጋሪና የተለየ ተጠቃሚ በመሆኑ በተጠያቂነት አብሮ መፈረጅ አለበት የሚባል ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ፈጽሞ የለም። ወያኔዎች ግን ከትግራይ ሕዝብ፣ በትግራይ ሕዝብ፣ ለትግራይ ሕዝብ ብቻ በታቀደ ዓላማ ላይ ተመስርተው በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የዘመቱ በመሆናቸው ከጭራ የቀጠነ ደንበር አስምሮ (ኢትዮጵያዊ አመለካከት ያላቸውን ግለሰቦች ሳይጨምር) ከዚህ ወዲያ ያሉትን አይመለከታቸውም ብሎ ለመለየት እንኳ በማይቻልበት ደረጃ ላይ መዳረሳችን ድብቅ አይደለም።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የወያኔዎች አምባሳደር አውሮፓ እየኖሩ ቅሬተ ነገራቸውን ለማጠናቀቅ ከሚከናውኑ ይልቅ የአካባቢው አገሮች ከገጠሟቸው ከባድ ችግር ጠቃሚ ትምህርትና ልምድ ቢቀላውጡ ይጠቅማቸው ነበር። ለምሳሌም የጀርመን ናዚዎች በአይሁዳውያን ላይ፣ የኢጣሊያን ፋሽስቶችም ቅኝ በገዟቸው አገሮችና ሕዝቦች ላይ በፈጸሟቸው በዘረኝነት ላይ የተመሰረቱ ዘግናኝ ድርጊቶች እንወክለዋለን የሚሉትን ሕዝብ በተወሳ ቁጥር አንገቱን ሲደፋ እንዲኖር የሚያደርግ ሐፍረትና እስክ ልጅ ልጁ ሲከፍል እንዲኖር የተገደደበት እዳ አሸክመውት እንዳለፉ ከበቂ በላይ የሆነ ማረጋገጫ ይመስለኛል። ያውም የሁለቱም ወንጀል አገር ማጥፋትን ሳይጨምር ማለት ነው። የወያኔዎች እቅድ ግን የብዙሐኑን እናት አገር ከማጥፋት ጀምሮ በዓላማም ሆነ በግብር ከእነዚያ ፋሽስቶችና ናዚዎች ድርጊት በፍጹም የማይለይ በመሆኑ አብሮ ሲዘምት የኖረውን የትግራይን ሕዝብ ከተጠያቂነት እዳ ነጻ የሚያደርግ አንዳችም መንገድ የለም። ስለዚህ ለትግራይ ሕዝብ የምለግሰው አማራጭ የሌለው ጥቃሚ ምክር ቢኖር ያውም ከተቀበለው ነው በእርግጥም ከወያኔዎች ጋር ግንኙነት የለኝም ካለ ከአፈቀላጤዎቹ የቃላት ግርዶሽ በመውጣት እርሱ አንጠላጥሎ ከዚህ ደረጃ ላይ ያደረሳቸውን የአገርና የሕዝብ ጠላቶች ዘርጥጦ በመጣል መገላገልና እራሱን ነጻ ማውጣት ብቻ ነው።

7. ከዚህ ቀጥሎ "ታዲያ በዚህ ሁኔታ የትግራ ህዝብ ምን ያድርግ ነው የሚሉት?" ያሉትን ጥያቄ ልመስላቸው። ጥያቄው መሠረታዊ ጥያቄ በመሆኑ በዚያው መጠን መሠረታዊ መልስ የሚያስፈልገው ይመስለኛል። በመሆኑም የትግራይ ሕዝብ ማድረግ የሚገባውን ለመግለጽ በቅድሚያ ልጆቹ ሲያካሂዱ በኖሩት ሁለንተናዊ የማጥፋት ዘመቻና ርብርቦሽ ላይ መተማመንን ይጠይቃል። ባለፈው ጽሁፌ 18 ዓመታት ቀላል ጊዜ እንዳልሆነ መግለጼን አስታውሳለሁ። እንዲያውም ከዚህም አልፎ ሁለንተናዊ ድጋፍ እየሰጠ ከዚህ ደረጃ ላይ ያደረሳቸው ልጆቹ እናት አገሩን ለማጥፋትና ከወገኑ ጋር በቀላሉ የማይደርቅ ደም አቃብተው እስከ መጨረሻው ለማቆራረጥ አቅደው የተነሱበትን 35ኛ ዓመት በራሱ ከተማ አክብረውለታል። በእዚህ ረጅም የምስቅልቅል ዓመታት ልጆቹ በተቀነባበረ መልኩ ሲያካሂዱ የኖሩትን ውድመት፣ ጥፋትና እልቂት በዝርዝር ለመግለጽ ብዙ ገጽ የሚወጣው መድብል በመሆኑ እሱን ለታሪክ ባለሞያዎች ትቸ "ለመሆኑ በእናት አገርህና በወገንህ ላይ ይህን ሁሉ ጥፋት በማድረስ ላይ ያሉትን ልጆችህን የኢትዮጵያ መንግሥት ናቸው ብልህ ታምናለህን? አዎ! ካልክ ደግም ከእነማን ጋር አወዳድረህ ነው? የሚል ጥያቄ አቅርቤለት እንደነበር አስታውሳለሁ። ስለዚህ ማድረግ የሚገባው የመጀመሪያ እርምጃ፣

1. ጥያቄው ካተኮረበት ዓብይ መልዕክት አንጻር ኢትዮጵያዊ ሐላፊነትን ያገናዘበ ሁነኛ መልስ መስጠት ነው‹

2. የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆችህ የሁላችንም የሆነችውን እናት አገር እያጠፉብንና እኛንም መኖሪያ ቀርቶ መቀበሪያ አፈር እያሳጡን ስለሆነ ሐላፊነቱ የማይመለከትህና ጥፋቷ የማይጎዳህ ይመስል የሩቅ ተመልካችና የተለየ ተጠቃሚ መስለህ ከምትታይ ይልቅ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ ተባብረን ልናድናት ይገባል ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ሁነኛ መልስ መስጠት አለበት፣



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

3. ወያኔዎች ይህን ያህል ዓመት ተደላድለው የኖሩትና ይህን ሁሉ ግፍና በደል የሚፈጽሙት በእሱ ሁለነናዊ ድጋፍና የማጥፊያ መሳሪያነት ነው። ይህን ደግም እርሱም ቢሆን ጠንቅቆ ያውቃል። ስለዚህ ምን ማደርግ አለበት ለተሰኘው የዶ/ሩ ጥያቄ መደምደሚያው መልስ የእስከአሁኑ ስለሚበቃ ካሁን በኋላ ለልጆቹ መሳሪያ ሆኖ ማድረግ የማይገባውን ከማድረግ ጨርሶ መታቀብ አለበት። ይኸም ብቻ ሳይሆን እናት አገሩን ባጠፉበት፣ ከወገኑ ጋር ደም ባቃቡትና በአገሪቱና በሕዝቧ ላይ በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ሁለንተናዊ ምስቅልቅል በፈጠሩት ጠላቶቹ ላይ ዘምቶ ማንበርከክ ነው። በእርግጥ እንዲህ ያለውን እርምጃ ከወሰደ ያሉትን ጥላቻና ቅራኔዎች አርግቦ፤ የተቀባውን ደም አጽድቶና ሆድና ጀርባ የሆነባቸውን ችግሮች ሁሉ በውል ፈቶ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አዲስ የአብሮነት ተሐድሶ ህይወት ለመገንባት ያስችለዋል ብየ በጽኑዕ አምናለሁ። ለእነዚህ ጥያቄዎች ሁነኛ መልስ የማይሰጥ መከላከል ግን ጉንጭ አልፋ ከንቱ ጨኸት እንጅ ክሮ ሊበጠስ ለተቃረበው መሠረታዊ ቅራኔ መፍትሄ ማግኘት ማለት አይደለም።

ይህን ርዕስ የማጠቃልለው በሁሉም ታድለው የተፈጠሩት አባቶቻችን የአገራቸው ስትራተጂያዊ ጠላቶች ምን ያህል ሲፈታተኗቸው እንደኖሩ የእነሱን ሁለንተናዊ ባህሪይ የሚወርስ ትውልድ የተካን መስሏቸው አስተላልፈውለት ያለፉትን ጥልቅ መልዕክት ያለው አባባል በመጥቀስ ነው። እንደሚታወቀው የአገራችን ችግር ከመልካ ምድራዊ አቀማመጧ፣ ከተፈጥሮ ሐብቷና ከሕዝቧ የረጅም ዘመናት የተጋድሎ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ችግር ደግሞ ከምዕራባውያን ቅኝ ገዥወች ጋር ብቻም ሳይሆን በዙሪያ ገቧ ከሚገኙ የአባይ ወንዝ ብቸኛ ተጥቃሚ ሆነው ለመኖር ከሚፈልጉ የአረብ አገሮችም ጋር ጦር ሲያማዝዝ የኖረ መሆኑን የማይረዳ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም። በተለይም ኢትዮጵያን በልዩ ልዩ ችግር አዳክመው በብሔራዊ አገርነቷ እንዳትቀጥል በማድረግ የተፈጥሮ ሕብቷን ያለምንም ተከላካይ ኃይል ተጠቃሚ ለመሆን ሲጥሩ የሚኖሩት አረቦች አገሪቱ የተረጋጋ ሰላም አግንታ በልማት ግንባታ ላይ እንዳታተኩር ቀጣይ የሆኑችግሮች እየፈጠሩ በየጊዜው ሲያውኳት እንደኖሩ በውል ይታወቃል። የረጅም ዘመን ጥረታቸው ወደእኛ ዘመን ተሸጋግሮ ሻቢያዎችና ወያኔዎችን ለዚህ ማብቃታቸው ለዋቢነት የበቃ ነው። እነዚህን ሁሉ ጠንቅቀው የሚያውቁት አይበገሬ ጀግኖች ደግሞ የመጋፋት እቅዳቸውን ወደስጋት ለውጠው ያስጨነቁበት ወቅት እንደነበርም ታሪክ መዝግቦት ያለፈ ሐቅ ነው። በአለመታደል በአሁኑ ወቅት ግን በሯን ወለል አድርገው የሚከፍቱና እየበልቱ የሚያከፋፍሉ የአገር ሰው መሳይ የአገር ጠላቶች ስለተቀፈቀፉ ሲመኙት የኖሩት አመች ሁኔት የተመቻቸላቸው የአገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች ፊት ለፊት ዘምተው ያጡትን እድልና ድል በሰላማዊ መንገድ ሰተት ብለው ገብተው ከዳር እስከ ማህል እየተረከቧት ነው። አርቀው የሚያስቡት ብልሆቹ አባቶቻችን ግን ትውልዱ አንድ ቀን እንዲህ ያለው ፈተና እንዳይገጥመው በማሰብ አስቀድመው የሰጡት ብርቱ ማስጠንቀቂያ ነበር። ጥቅሱ በጋራ ስለምነጨነቅላት እናት አገር ታሪካዊ ጠላቶቻችን የተነገረ እንጅ ከእምነት ጋር የተያያዘ በአለመሆኑ የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ ወገኖቸ በጠየመ ትርጉም እንዳያዩብኝ በቅድሚያ ማሳሰብ እወዳለሁ። ከጠላቶቻችን በርካታ ሙከራዎች አንዱም አህመድ ግራኝ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የተባለ ወራሪ አደራጅተው በማዝመት በሕዝብ ሕይወት ላይ ያደረሰው እልቂትና በሐገር ሐብትና ቅርስ ላይ ያደረሰው ውድመት ነበር። ይህን ጠንቅቀው የሚያውቁት አባቶቻችን፣

"በዘመነ ግራኝ ምን እንጀራ ጠፍቶ

አረብ ሌት ይበላል እንኳን ቀን አግኝቶ" ብለው ገልጸውት ነበር።

ለአሁኑ ትውልድ ፈታኝ ፈተና ሆኖ የቀረበለትም ይኸው ነው። ትውልዱ ግን በራሱ ታሪክ የመኩራትና ከአባቶቹ የተጋድሎ ታሪክ የመማር ታድሎ የሌለው ድሐ ትውልድ በመሆኑ እነዚህን ሁሉ መለስ ብሎ ሊያዘክራቸውና እራሱን አዘጋጅቶ የራሱ የሆኑትን ሁሉ ሊያስከብርባቸው አልቻለም። አባቶቻችን አስተላልፈውልን ያለፉት መልዕክት ግን አረቦች በሯን ወላል አድርገው የሚከፍቱላቸውና ፈቅደው የሚያስረክቧቸው የልጅ ጠላቶች አግኝተው ቀርቶ በአሉበት ሆነው እንኳ ስለማይተኙልን እኛም ልንዘናጋላቸውና ምኞታቸውን ማሳካት የሚችሉበት እድል ልንሰጣቸው አይገባም ማለታቸው ነበር። ይኸውና የጊዜ አጋጣሚ ሆኖ አህመድ ግራኝን ለዚያ ያበቁ ጠላቶቻችን የአህመድ ግራኝን ዓላማ ያነገቡና ግብሩን የወርሱ ልጆች ስላገኙ ምን በማድረግ እንዳሉ በገሐድ እያየን ነው። ኢትዮጵያን በመቆጣጠር አባይና ጣናን በብቸኝነት ለመጠቀም ሲድሁ የኖሩት ገብያች ይኸውና በወያኔ ጊዜ **ቀን አግኝተው** የአባይና ጣና ምንጭ በሆነችው ባህርዳር ላይ የኢንዱስትሪ መንደር ለመመሥረት መሬት ገዝተዋል እየተባለ ነው።

በአጠቃላይ ደንበሩን ተሻግሮ ከእናት አገራችን ጓዳና ማጀት ድረስ ሰተት ብሎ የገባው ችግር በውስጡ ብዙ ሲያሳምም የሚኖር መርዝና ሲያማዝዝ የሚኖር መዘዝ ያለበት ነው። ለሁልጊዜም ሲያማቅቅና ሲያሸቅቅ የሚኖር ውስብስብ ችግርም ያለበት ነው። እዚህ ላይ በውል መረዳት ያለብን በትላንቶቹና በዛሬዎቹ ጠላቶቻችንና በአቀረቡልን የችግር መስተንግዶ መካከል ልዩነት ኖሮ ሳይሆን እኛ የአባቶቻችንን ባህሪይ የወረስንና ለአደራ የበቃን ልጆች ሆነን በአለመገኘታችን ብቻ ነው። መፍትሄውም እዚያ ማዶ ስለአሉት አረቦች መቃለት ሳይሆን በውስጣችን የበቀሉትን አረሞች እንዴት ነቅለን እንደምናድርቅ መዘጋጀትና ለአረሞች መንቀያና ለሾሆች መመንጠሪያ የሚሆኑንን መሳሪያዎች አዘጋጅቶ መዝመት ነው። ለዚህ ደግም የግድ የትልቅ መሳሪያን መገኘት ይጠይቃል ወይም ይፈልጋል ማለት ብቻ አይደለም። ህሊናዊ ዝግጅቱና አካላዊ ብቃቱ እስከለ ድረስ አካፋና ዶማው፣ ማጭድና ቢላዋው፣ አጣናና ከንተሮው ሁሉ አረሞችን ለመንቀልና እሾሆችን ለመመንጠር ብቃት ያላቸው መሳሪያዎች ናቸው። እራስን ለዚህ ሳያዘጋጁና እነዚህን ሳያዘጋጁ ሲጯጯሁ መኖር ግን እየደነዙና ጨርሶም እየበደኑ መሄድ እንጅ እየበሰሉና እየተሳሉ መሄድ አይደለም። ውሃ እንኳ በልሙ መሬት ይቆርጣል ይባላል። እኛ ግን ከውሃው የበለጠ ባለብዙ አፍ ስለት እያለን በስለቱ ቆርጠን በመቁረጥ የእነዚያም አንጀት አብሮ እንዲቆረጥ ማድረግ እንኳ ባንችል በዶማው እየገዘገዝን የምናቆስልና እየገዘግዝ የምንጥል አልሆነም። ከዚህ ይልቅ እኛው እርስ በርሳችን እየተገዛገዝን በመኖሩ ተስለን ቀጥለንበታል ማለት ነው። በዚህም ምክንያት በእጅጉ የተናቁት አገር ሻሎች ሎሌነት እንኳ እንደጀግንነት ተቆጥሮ በእጅጉ እየናቁን ነው። ወደፊትም ቢሆን የቅርቡ የሩቁን ሰው



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ደባይት ከሚጠበቅ ይልቅ ሁሉም በነፍስ ወከፍ የየራሱን ማደባያ መሳሪያ ይዞ በመውጣት ለማደባየት እራሱን አዘጋጅቶ ከወጣ ነገሮች ፈጥነው መልካቸውን እንደሚለውጡ እርግጠኛ ነኝ። እኔ እንደሚገባኝ ለሰው ልጅ ትልቁ ጠላቱ በራስ የመተማመን እጦቱና የማይበልጠውን ጠላቱን ይበልጠኛል ብሎ በስነ ልቦናው መማረኩ ነው። የዚህ ችግር ከሌለ መሳሪያ ግን በሁለት ተወዳዳሪ ቡድኖች መካከል ማህል ሜዳ ላይ እንደተቀመጠች ኳስ የሚታይ ነው። ምክንያቱም ጨዋታው ከተጀመረ በኋላ በኳሷ የሚያዙባት አጠቃቀሙን የሚያውቁበት ባለሞያዎች እንጅ ሜዳው ውስጥ የገቡት ሁሉ አይሆኑምና ነው። ከታሪካዊ ልምዳችን የምንማረውም ይህንን እውነታ ነው። የጠላቱን እግር እየለካ ቁጭቱን ለመወጣት አጋጣሚን በመጠበቅ ላይ ያለ ልበ ሙሉ ጀግና፣

"ኧረ ተይ ክላሽን ተኳሽሽን ንገሪኝ

ተሸካሚሽ ሁሉ እያንገራገረኝ" እያለ የሚያንጎራጉረውም የግብይይቱ እለት ምን ሊያደርግ እንደሚችል ልቦናው ስለሚያውቅ ነው። እንዲያውም እንዲህ ያለው ሕዝባዊ ክንድ የተሰነዘርበት እርምጃ ከዚያ በኋላ በጤናማው መሬታችን ላይ የችግር አረም እየዘሩ መርዘኛ እሾህ ለማምረት የሚጥሩ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ጠላቶች ሁሉ ለአንዴና ለመጨርሻ ጌዜ እንዲያከትምላቸው ማድረግ የሚያስቾል ስር ነቀል እርምጃ ነው የሚል እምነት አለኝ።

“የሰው ዘር ዳኛ የሆነው አምልክ ፍርድ አያሳጣን!”

“ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ “

(ክፍል አራት ይቀጥላል)



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com